36960.doc

38572.doc

38681.doc

40624.doc

41857.doc

42361.doc

42594.doc

42682.doc

42749.doc

42766.doc

42805.doc

43248.doc

43271.doc

43417.doc

43614.doc

44203.doc

44449.doc

44800-11-6-02.doc

45167.doc

የሰ/መ/ቁ 36960

ጥቅምት 25 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

አመልካች፡- የአቶ ተገኔ ሚኮ ወራሾች ሞግዚት ወ/ሮ ወሰኔ ሀይሉ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ብርሣም ተክሉ ጠበቃ አቶ ኪሮስ ገብሩ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 27809 ጥር 3 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝና የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 45286 ህዳር 19 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ሚያዚያ 1 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ አመልካቾች አውራሻቸው ሟች አቶ ተገኔ ሚኮ ከተጠሪ ጋር የካቲት 15 ቀን 1987 ዓ.መ የዕርቀ ስምምነት የፈፀሙና ስምምነታቸውም የካቲት 20 ቀን 87 ዓ.ም የፀደቀ መሆኑን ገለፀው ተጠሪ በዕርቅ ስምምነቱ መሠረት ያልፈፀመች ስለሆነ በዕርቅ ስምምነቱ መሠረት እንድትፈፅም ትዕዛዝ ይሰጥልን በማለት ያቀረቡት የአፈፃፀም ክስ ነው፡፡ ተጠሪ የአፈፃፀም ክስ ዕርቁ ከፀደቀ ከአስር ዓመት በኋላ የቀረበ ስለሆነ በይርጋ ይታገዳል የሚል መቃወሚያ አቀርበዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካቾች ዕርቁ ከፀደቀ አስር ዓመት ከአምስት ወር ከሆነው በኋላ በመሆኑ የአፈፃፀም ክሱ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 384(ሀ) መሠረት በይርጋ ይታገዳል በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቀርበው የከፍተኛው ፍርድ ቤት የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 384(ሀ) የተደነገገው የይርጋ ጊዜ ገድቦ አፈፃፀም ክስ ካቀረበ በኋላ በተለያየ ምክንያት የአፈፃፀም ክርክሩ

በተቋረጠባቸው ጉዳዮች ብቻ ተፈፃሚነት ያለው እንጅ ጭራሽ የአፈፃፀም ክስ ባልቀረበባቸው ጉዳዮች ተፈፃሚነት የለውም በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል። ተጠሪ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራለ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቀርበዋል። ችሎቱም የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የአመልካቾች የአፈፃፀም ክስ የይርጋ የጊዜ ገደብ አላለፈበትም በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የአፈፃፀም ክሱ የይርጋ ጊዜ ገደቡ አልፎበታል በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ አፅንቷል።

አመልካቾች በሰበር አቤቱታቸው የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት። የይርጋ ጊዜው መሰላት ያለበት የዕርቅ ስምምነቱ ከፀደቀበት የካቲት 20 ቀን 1987 ዓ.ም ጀምሮ መሆን የለበትም። የአመልካቾች አውራሽ ሟች አቶ ተገኔ ሚኮ ተጠሪ በፍርድ ቤት በፀደቀው የዕርቅ ስምምነት መሠረት ገንዘቡን ያልከፈሉቻቸው መሆኑን በመግለፅ ፍርድ ቤቱ በዕርቁ መሠረት እንዲያስፈፅምላቸው ዕርቁን ላፀደቀው ፍርድ ቤት ማመልከቻ አቅርበው ፍርድ ቤቱ ህዳር 10 ቀን 1988 ዓ.ም ትዕዛዝ ሰጥቶበታል። ስለዚህ ይርጋው የተቋረጠ ስለሆነ ከህዳር 10 ቀን 1988 ዓ.ም ጀምሮ

የሰ/መ/ቁ 38572

ጥቅምት 17 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት አቶ ናሆም ሸዋንግዛው

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ወ/ሮ ሀና አባይ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍታብሔር ይግባኝ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች ሰኔ 9 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ የአሁን ተጠሪ በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በከሳሽነት ቀርቦ አቶ ሐጎስ ተድላ ከንፋስ ስልክ ቅርንጫፍ ለወሰዱት ብር 75,000 (ሰባ አምስት ሺ ብር) ንብረትነቱ የተበዳሪው የአቶ ሀሰን አብደላ የሆነ የሠሌዳ ቁጥሩ 3-16015 እና የተሳቢው መለያ ቁጥር 3-03383 የሆነ መኪና በመያዣነት ይዘናል፡፡ ተጠሪ እና ተበዳሪው አቶ ሐጎስ ተድላ መያዣው የመድን ዋስትና እንደገባለት በተስማሙት መሠረት በመያዣነት የተያዘው መኪና በተከሳሽ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ምስራቅ አብይ ቅርንጫፍ ብር 350,000 (ሦስት መቶ ሀምሳ ሺ ብር) ተገምቶ ኢንሹራንስ መድን ተገብቶ የአረቦን ክፍያ ስንከፍል ቆይተናል፡፡ የመድን ውሉ እየታደሰ ፀንቶ ባለበት ጊዜ

ህዳር 28 ቀን 1988 ዓ.ም መኪናው በደረሰበት የመገልበጥ አደጋ ከጥቅም ውጭ ስለሆነና ተከሳሽ (አመልካች) ከመያዣው ግምት ብር 350,000 (ሦስት መቶ ሀምሳ ሺ ብር) እንዲከፍል ብንጠይቀው ፈቃደኛ ስላልሆነ እና ተበዳሪው ብድሩን ያልከፈሉ በመሆኑ በመያዣነት የያዝነውን የመድን ዋስትና የገባለትን መኪና ዋጋ እንዲከፍሉ ይወሰንልን በማለት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ከተጠሪ ጋር ቀጥተኛ የሆነ የውል ግንኙነት ስለሌለኝ ክስ የማቅረብ ችሎታ የለውም፡፡ መኪናው የተገለበጠው አሽከርካሪው መሪ እንቢ ብሎኝ ነው በማለት ያቀረቡት መግለጫ በቴክኒክ ማስረጃ ያልተረጋገጠ በመሆኑ ሀላፊነት የለብንም፡፡ በመኪናው ላይ የደረሰው ጉዳት በባለሙያ አልተረጋገጠም፡፡ መክፈልም ካለብን ሰባ አምስት ሺ ብር ነው የሚሉ መከራከሪያዎችን አቅርቧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በአመልካች በኩል የቀረቡትን መከራከሪያዎች ውደቅ በማድረግ አመልካች ለተጠሪ መያዣው በአደጋ በመውደሙ ምክያት የደረሰበትን ጠቅላላ ጉዳት ብር 350,000 (ሦስት መቶ ሀሣሳ ሺ ብር) ከህዳር 8 ቀን 1988 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርቦ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የጉዳቱ መጠን አልተረጋገጠም በሚልና በሌሎች ነጥቦች የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ በመሻር ጉዳዩ እንደገና ታይቶ እንዲወሰን ጭብጦችን በመለየት ለሥር ፍርድ ቤት መልሷል፡፡ ተጠሪ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፍታብሔር ይግባኝ ችሎት አቅርቦ ችሎቱ የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች ይህንን ውሣኔ በመቃወም የቀረበው የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በተበደረው ብድሩ ያልተከፈለው መሆኑን ሣያረጋግጥ ክስ እንዲያቀርብና እንዲከራከር መደረጉ መሠረታዊ የሆኑ የኢንሹራንስ መርሆችና ዓላማ የሚቃረን ነው፡፡ ተጠሪ ተበዳሪው ከተበደረው ውስጥ የከፈለውን ያልከፈለውን ለይቶ አላቀረበም ተጠሪ ያበደረው 75,000 (ሰባ አምስት ሺ ብር) ሆኖ እያለ ተገቢ ያልሆነ ክፍያ ጠይቋል ተጠሪ ብድሩ ባለመከፈሉ የነበረውን ወለድ እና ትርፍ መጠየቁ ተገቢ አይደለም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍታብሔር ይግባኝ ችሎት አግባብነት ያላቸውን የፍታብሔር ህግ እና የንግድ ህግ በመተላለፍ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት በፅሑፍ ያመለከተ ሲሆን ይህንኑ የሚያጠናክር የቃል ክርክር አቅርቧል ተጠሪ በበኩሉ ተበዳሪው እዳውን በወቅቱ ባለመክፈሉ ምክንያት ወለዱና ሌሎች በብድሩ አለመከፈል ምክንያት መከፈል ያለበት ገንዘብ ሲታሰብ ብር 350,000 (ሦስት መቶ ሀምሳ ሺ ብር) ጉዳት የደረሰብን መሆኑን አስረድተናል፡፡ ተጠሪ የመድን ሽፋን ለማግኘት ከአመልካች ጋር የመድን ውል እንደገባ ያደረገውና የአረቦን ክፍያ ሲከፍል የኖረው ለተበዳሪው ለሰጠው ብር 75,000 (ሰባ አምስት ሺ ብር) ሣይሆን ይኸ ብድር በወቅቱ ባይከፈል ለብድሩ መያዣ ለሆነውና ዋጋው ብር 350,000 (ሦስት መቶ ሀምሳ ሺ ብር) ለሆነው በመያዣነት ለያዝነው መኪና ነው፡፡ የጠየቅነው ገንዘብ በመድን ውሉ ከተሰጠው ሽፋን የበለጠ አይደለም ስለዚህ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ያለው ክርክር ተጠሪ ላበደረው ብድር በመያዣነት የያዘው መኪና ለሚደርሰው ጉዳት እስከ ብር 350,000 አመልካች የመድን ሽፋን ሊሰጥ፣ መኪናውን ያስያዘው ሰው ወይም

ተጠሪ በየጊዜው መክፈል የሚገባውን አረቦን ሲከፍሉ ነው። ተጠሪ የመድን ሽፋን ለተገባለት ንብረት መከፈል የሚገባውን አረቦን ያለ ማቋረጥ የከፈለ መሆኑንና በዚህ ሒደት መኪናው አደጋ የደረሰበት መሆኑ የሚያከራክር አይደለም።

አመልካች መኪናው ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጭ አልሆነም የሚል መከራከሪያ ያቀረበ ቢሆንም ተጠሪ ካቀረበው ማስረጃ የተሻለ ማስረጃ በማቅረብ ክርክሩን ያላስረዳ መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል። ስለዚህ በዚህ በኩል አመልካች የሚያቀርበው ክርክር ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም። ተጠሪ የመኪናው ባለቤት ለሆኑት ተበዳሪ ብር 75,000 (ሰባ አምስት ሺ ብር) ሲያበድሩ ለብድሩ አከፋፈል ዋስትና ይሆነው ዘንድ ግምቱ 350,000 (ሦስት መቶ ሀምሳ ሺ ብር) የሆነ መኪና በመያዣነት ይዟል። አመልካች ላበደረው ብድር አከፋፈል ዋስተና እንዲሆነው በመያዣነት በያዘው ንብረት ላይ ያለው መብት ብድሩ ባለመከፈሉ ቀሪ የሆነ ዋናው ገንዘብ፣ ይኸ ብድር በብድር ውሉ መሠረት ባለመከፈሉ የሚወልደው ወለድ፣ የወለድ ወለድ መቀጫና ሌሎች ወጭዎችን ሁሉ ባለመከፈላቸው መያዣውን ሸጦ ገቢ የማድረግ መብቱን የሚያጠቃልል መሆኑና ጠቅላላ ጣሪያው በመያዣ ውሉ የተገለፀው የገንዘብ መጠን እንደሆነ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2858 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል።

ተጠሪ ተበዳሪው ብድሩን ባለመክፈሉ ምክንያት ብር 350,000 (ሦስት መቶ ሀምሳ ሺ ብር) ዋናው ብድር ወለድና ሌሎች ክፍያዎች ከተበዳሪው እንደሚፈልግ በሥር ፍርድ ቤት አስረድቷል። ተጠሪ ለዚህ ገንዘብ አከፋፈል ይረዳው ዘንድ በመያዣነት የያዘው ንብረት የነበረ መሆኑ ተረጋግጧል። ተጠሪ በመያዣነት የያዘው ንብረት በባህሪው ተንቀሣቃሽና ለአደጋ ተጋላጭ መሆኑን በመረዳት በመያዣነት የያዘውን ንብረት በብር 350,000 (ሦስት መቶ ሀምሳ ሺ ብር) የመድን ሽፋን እንድገባለት

አድርጓል፡፡ ይህንንም ያደረገው ተጠሪ ያበደረውን ገንዘብ እና ወለድና ሌሎች ክፍያዎች የማስመለስ እድሉን ለማስፋት እና እርግጠኛ ለመሆን ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ አመልካች እንድከፍለው የጠየቀውና የሥር ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ለተጠሪ ብር 350,000 (ሦስት መቶ ሀምሳ ሺ ብር) ከህዳር 8 ቀን 1988 ዓ.ም ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍል የወሰኑት የንግድ ህግ ቁጥር 678 ድንጋጌ መሠረት በማድረግና የኢንሹራንስ ውሉን መሠረት በማድረግ በመሆኑ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስላላገኘነው በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት አፅንተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍታብሔር ይግባኝ ችሎትና በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይኸ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሠ/መ/ቁ 38681

ጥቅምት 3 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሀይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - አልቀረበም

ተጠሪ፡- እማሆይ ፀሐይቱ አምበሉ - ወኪል ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁጥር 12269 ሰኔ 29 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመጽናቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች ቅሬታ በማቀረቡ ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በምዕራብ ጉጃም ዞን አስተዳደር ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ በጅጅጋ ከተማ በ500 ካ/ሜትር ቦታ ላይ ያረፈውን ቤት ከሳሽና ሟች ባለቤቱ ቁስ አለሙ ከበደ ወ/ሮ አስካለ አድማሱ ከተባሉት ግለሰብ ገዝተን ባለሀብትነቱን በባለቤቱ ስም አዙረን ከዚያም ባለቤቱ ሲሞቱ በከሳሽ ስም ዞሮ ከነሐሴ 1975 እስከ ሰኔ 1998 ዓ.ም ድረስ ከሳሽ ግብር እየከፈልኩ ለ23 ዓመት በባለሀብትነት ይገዙው የምገኝ ሲሆን ቤቱን መያዣ ለማድረግ የሚያበቃ ውክልና ሳይኖር ተከሳሽ መያዣ አድርጌዋለሁ በማለት በጨረታ ለመሸጥ የጋዜጣ ማስታወቂያ ያወጣ ስለሆነ

ባንኩ ቤቱን ለመሸጥ ከሕግ ወይንም ከውል የመነጨ መብት ሳይኖረው ሊሸጥ ስለማይችል መብት የለውም ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የከሳሽ ክስና ማስረጃም ለተከሳሽ ደርሶ በሰጠው መልስ ክስ የቀረበበትን ቤት ተከሳሽ በሐራጅ ለመሸጥ የተነሳው ከአቶ ምንውየለት ዓለሙ ጋር ባደረገው የብድር ውል ተበዳሪው መጋቢት 4 ቀን 1987 ዓ.ም ለንግድ ሥራ ማስፋፊያ የሚያውሉት ብር 30 ሺህ በብድር ሲወስዱ መያዣ ስለሰጡ ነው፡፡ ይህም የሆነው ቤቱ በተበዳሪው ስም የተመዘገበ ስለመሆኑና ዕዳና ዕገዳ የሌለበት ስለመሆኑም የጅጋ ከተማ ማዘጋጃ ቤት በሰጠው ማረጋገጫ መሠረትና መያዣውም በማዘጋጃ ቤቱ በመመዝገቡ ነው፡፡ ስለሆነም ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የምዕራብ ጐጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክር የተነሳበትን ቤት ከሳሽና ባለቤታቸው የገዙት ነው ወይንስ የተበዳሪው የአቶ ምንውየለት ዓለሙ ነው የሚል ጭብጥ መስርቶ ጉዳዩን በመመርመር ከሳሽ ከባለቤታቸው ቁስ ዓለሙ በላይ ጋር በትዳር አብረው በነበሩ ጊዜ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ከወ/ሮ አስካለ አድማሱ ላይ ገዝተናል ቢሉም ይህንን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ካለማቅረባቸውም በላይ ስም ንብረቱም ከወ/ሮ አስካለ አድማሱ ወደ ቁስ ዓለሙ በላይ ስለመዞሩ የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡ አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ንብረቱ ባለበት አገር በሚገኘው በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ካልተጻፈ በስተቀር በ3ኛ ወገኖች ዘንድ ውጤት እንደሌለው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2878 ላይ የተመለከተ ስለሆነ ከሳሽም በስማቸው ከ1975-1998 ዓ.ም ግብር የከፈሉ ስለመሆኑ ቢረጋገጥም የሽያጭ ውሉ ሥልጣን ባለው አካል ካልተመዘገበ ውጤት የሌለው ነው ካለ በኋላ አቶ ምንውየለት ዓለሙ ከተከሳሽ ገንዘብ ሲበደሩ ይህንኑ ቤት አስይዘው መሆኑን እንደዚሁም የጅጋ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ክርክር የተነሳበት ቤት የአቶ ምንውየለት ዓለሙ መሆኑን ያረጋገጠ

ስለሆነ ከሳሽ የቤቱ ባለቤት ስለሆንኩ ተከሳሽ መብት የለውም ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረቡት ክስ የማስረጃ ድጋፍ የለውም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ከሳሽ በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ጠቅላይ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ለክርክሩ መነሻ መክንያት የሆነውን ቤት የይግባኝ ባይ ባለቤት የነበሩት ቂስ ዓለሙ በላይ ከወ/ሮ አስካለ አድማሱ ገዝተው ስም ንብረቱ መዞሩንና በስማቸው መመዝገቡን በደረሰኝ ቀጥር 29764 በሆነ ለውል ማስመዝገቢያ መክፈል የሚገባውን በማስከፈል የመዘገበ መሆኑን የጅጋ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የሰጠው ማስረጃ ያስረዳል፡፡ ከዚያ በኋላም ይግባኝ ባይና ባለቤታቸው የከተማ ቦታ ኪራይ ለመንግስት እየከፈሉ እስከ 1977 ዓ.ም ይዘውት እደቆዩና ከዚያም ቂስ ዓለሙ በላይ ሲሞቱ ይግባኝ ባይ በስማቸው በማዛወር የከተማ ቦታ ኪራይ ለመንግስት ሲከፍሉ እንደነበር የቀረቡት ማስረጃዎች ያረጋግጣሉ ካለ በኋላ በሌላ በኩልም መ/ሰጭ ቤቱ የተበዳሪው የአቶ ምንውየለት ዓለሙ መሆኑን ያቀረበው ማስረጃ የጅጋ ከተማ ልዩ ቀበሌ ፍርድ ሸንጎ በማስረጃ አረጋግጦ በመስጠቱና የከተማው ማዘጋጃ ቤትም የተበዳሪው ቤት መሆኑን በማረጋገጥ የጻፈውን ደብዳቤ መነሻ በማድረግ ነው፡፡ ሆኖም ግን ቤቱ የተበዳሪው ቢሆን ኖሮ ጅጋ ከተማ ማዘጋጃ ቤት እያለ የከተማ ቤትና ቦታን የማስተዳደርና የመመዝገብ ሥራ እንደሚሰራ እየታወቀ ከዚሁ አካል ቤቱ የተበዳሪው መሆኑን ማረጋገጥ እየተገባ በቀበሌ ፍርድ ሸንጎ በኩል ይህንን ማረጋገጥ ሥልጣን አለው ለማለት አይቻልም፡፡ የጅጋ ከተማ ማዘጋጃ ቤትም ክርክር የተነሳበት ቤት የተበዳሪው መሆኑን ቢገልጽም የመያዣ ውሉን ተቀብሎ ስለመመዝገቡ ያላረጋገጠ ስለሆነ የመያዣ ውሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3052 አግባብ መሠረት ተመዘግቧል ለማለት ስለማይቻል በዚህ ሁኔታ መ/ሰጪ ቤቱን መያዣ አድርጎታል ተብሎ የይግባኝ ባይ

መብት ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ በአግባቡ አይደለም በማለት የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር ቤትና ይዞታው የይግባኝ ባይ ነው ሲል ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

መ/ሰጭም (የአሁን አመልካች) በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታውን መርምሮ አመልካች ክርክር ባስነሳው ቤት ላይ የመያዣ መብት የለውም ተብሎ በአማራ ክልል ጠቅላይና በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት መወሰኑ ለሰበር ቀርቦ ሊታይ እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን የዚህን ሰበር ችሎት ምላሽ የሚሻው የጉዳዩ ጭብጥ ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት ላይ አመልካች የመያዣ መብት አለው? ወይንስ የለውም? የሚለው ነው፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3041 ላይ እንደተመለከተው የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ በቀጥታ ከሕግ፣ ከፍርድ ወይንም ከውል ሊመነጭ ይችላል፡፡ አንድ የመያዣ ንብረት በመያዣ ከተሰጠ በመብቱ ለመገልገል እንዲቻል መያዣው አግባብ ባለው አካል መመዝገብ እንዳለበትም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3052 ላይ ተመልክቷል፡፡

በዚህ ጉዳይ አቶ ምንውየለት ዓለሙ የተባሉት ተበዳሪ ከአመልካች ላይ ብር 30ሺህ ሲበደሩ በጅጋ ከተማ ቀበሌ 01 ክልል የሚገኘውንና ቁጥር 835 የሆነውን ቤት በመያዣነት ሲያቀርቡ የከተማው ማዘጋጃ ቤት ይሄው ቤት በተበዳሪው በአቶ ምንውየለት ዓለሙ ስም እንደተመዘገበና ዕዳና ዕገዳም እንደሌለበት ለአበዳሪው ባንክ (ለአመልካች) በማረጋገጥ መያዣውንም የመዘገበ ስለመሆኑ በምዕራብ ጐጃም ዞን

ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ አመልካች ባቀረበው ማስረጃ መረጋገጡን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች ክርክር ባስነሳው ቤት ላይ የመያዣ መብት የለውም ወደሚል መደምደሚያ ለመድረስ የቻለው ከፍ ብሎ እንደተመለከተው ብድሩ በሚሰጥበት ወቅት ቤቱ የተበዳሪው መሆኑን ያረጋገጠው የከተማው ማዘጋጃ ቤት ሳይሆን የቀበሌው ፍርድ ሸንጎ ሰለሆነ ይህ አካል ይህንን የማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን የለውም እንደዚሁም መያዣው ስለመመዘገቡ አልተረጋገጠም የሚሉ ምክንያቶችን መሠረት በማድረግ ነው፡፡

ሆኖም ግን የቀበሌው ፍርድ ሸንጎ የቤት ባለቤትነትን በማረጋገጥ ማስረጃ የመስጠት ሥልጣን የለውም ቢባል እንኳን ቤቱ በተበዳሪው ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝና ዕዳና ዕገዳም እንደሌለበት የከተማው ማዘጋጃ ቤት ከማረጋገጡም በላይ ተበዳሪው አቶ ምንውየለት ዓለሙ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከፍኖተሠላም ቅርንጫፍ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውንና ቤት በዋስትና አስይዘው ብር 30ሺህ ሲበደሩ መያዣውንም ተቀብሎ መመዝገቡንም የከተማው ማዘጋጃ ቤት ያረጋገጠ እንደመሆኑ መጠን ተበዳሪው የቤቱ ባለቤት ስለመሆኑ ሥልጣን ባለው አካል በተሰጠ ማስረጃ አልተረጋገጠም መያዣውም አልተመዘገበም መባሉ ተገቢነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩልም ተጠሪ የዚሁ ቤት ባለሀብት ስለመሆናቸው አጥብቀው የተከራከሩ ቢሆንም የንብረት ባለሀብትነት ከሕግ ወይንም ከውል የሚመነጭ ሲሆን ይህንኑ መሠረት አድርጎ በዚሁ ክርክር ባስነሳ ቤት ላይ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1195(1) መሠረት ከመንግስት አስተዳደር አካል ባለሀብትነታቸውን በማወቅ የተሰጠ የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ወይም ባለሀብትነትን የሚያሳይ ማስረጃ በማቅረብ ባለሀብትነታቸውን ያላረጋገጡ ስለሆነ በዚህ ሁኔታ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ተጠሪ የቤቱ ባለሀብት

ናቸው በማለት የሰጠው ውሳኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይህንኑ ውሳኔ ማጽናቱ የአመልካችን የመያዣ መብት የሚጻረርና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ 12269 ሰኔ 29 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንደዚሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ 32718 ሰኔ 29 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 348(1) መሠረት ሽረናል፡፡
2. የምዕራብ ጐጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 14676 የካቲት 27 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 348(1) መሠረት አጽንተናል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ.40624

ጥቅምት 12 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ መብራት ታደሰ ጠበቃ አቶ አድማሡ መዓዛ ቀረቡ

2. ወ/ሮ ትዕግስት ዘውዴ

3. አቶ አንተነህ ዘውዴ

4. አቶ ቢኒያም ዘውዴ

ተጠሪ፡- አቶ ኤፍሬም ዘውዴ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት መስከረም 13 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡ የክርክሩ መሠረታዊ መነሻ የአሁን ተጠሪ ሚች አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ ወላጅ እናቱን ወ/ሮ አድማስወርቅ ጥላሁንን አግብተው ሲኖሩ የተወለደ በመሆኑ የሚች አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ ልጅና ወራሽ መሆኑ በፍርድ እንዲረጋገጥለት ያቀረበውን አቤቱታና ማስረጃ በመመርመር ተጠሪ የሚች ዘውዴ በሱፈቃድ ልጅና ወራሽ ነው በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ይህንን ውሣኔ ከሰጠ በኋላ የአሁን አመልካቾች በተቃዋሚነት

ቀርበው ሟች አቶ ዘውዴ በእሱፈቃድ 1940 ዓ.ም ለትምህርት ወደ አሜሪካ ሄደው ለሰባት ዓመታት እዚያው የቆዩ ስለሆነ 1945 ተጠሪን ሊወስዱ አይችሉም። ከዚህ በተጨማሪ ሟች ዘውዴ በእሱፈቃድ ከሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪ ውጭ ሌላ ልጅ የሌላቸው መሆኑን ጥር 18 ቀን 1990 ዓ.ም ኑዛዜ ያደረጉ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ አቶ ኤፍሬም ዘውዴ (ተጠሪ) የሟች ልጅ ነው በማለት የሰጠውን ውሣኔ እንዲያነሣልን በማለት አመልክተዋል። ተጠሪ በበኩላቸው የአመልካቾች ፍርዱን ለመቃወም ያቀረቡት ማመልከቻ ደርሷቸው አቶ ዘውዴ በእሱፈቃድ 1944 ዓ.ም ተመልሰው በመምጣት ወ/ሮ አድማስወርቅ ሚስታቸውን ጠይቀው ተመልሰዋል። እኔም ተረግዤ ተወልጃለሁ። የመቃወም አመልካቾች የእኔ ወላጅ እናት ወ/ሮ አድማስወርቅ ጥላሁንና አቶ ዘውዴ በእሱፈቃድ በባልና ሚስትነት ተጋብተው አልኖሩም ብለው ባልተቃወሙበት ሁኔታ የሟች ልጅ ልጅ መሆኔ ህግ ግምት የሚያዝበትን ጉዳይ በምስክር ለማፍረስ ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል። ፍርድ ቤቱም የአመልካቾችንና የተጠሪን ማስረጃ ከሰማ በኋላ የተጠሪ ማስረጃ ሚዛን የሚደፋና ተዓማኒነት ያለው የአመልካቾች ማስረጃ ተዓማኒነት አጠራጣሪ መሆኑን በመግለፅ ቀደም ሲል የሰጠሁትን ውሣኔ የሚነሳበት ምክንያት የለም በማለት የአመልካቾችን መቃወሚያ ውድቅ አድርጎታል። አመልካቾች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበው የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኙን ሰርዞታል።

አመልካቾች ተጠሪ አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ አሜሪካን አገር ለትምህርት ሄደው ባሉበት ተወለድኩ ያሉ በመሆናቸውና በመጀመሪያ እኔ ከተወለድኩ በኋላ ለትምህርት ሄዱ ያሉ ሲሆን በኋላ በእረፍት መጥተው ነው የተረገዝኩት በማለት ያቀረቡት ክርክር የሥር ፍርድ ቤት ተቀብሎ መወሰኑ ተገቢ ባለመሆኑ አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ ተጠሪን ለማሣደግ ያደረጉት ተሣትፎ የሌለ በመሆኑና ተጠሪም ይህንን ያላስረዳ በመሆኑ

ከሁሉም በላይ አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ ባደረጉት ኑዛዜ ከሁለተኛ ሶስተኛ እና አራተኛ አመልካቾች ውጭ ልጅ የሌላቸው መሆኑን ያደረጉት ኑዛዜ በቂና አሳማኝ ማስረጃ ሆኖ እያለ ተጠሪ የሚች አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ ልጅ ነው ተብሎ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው እኔ የተወለድኩት በወላጅ እናቴና በሚች ዘውዴ በሱፈቃድ መካከል ህጋዊ ጋብቻ ባለበት ጊዜ ውስጥ በመሆኑ የሚች ልጅ መሆኔ የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ የተረጋገጠ ነው፡፡ አመልካቾች ይህንን የህግ ግምት ለማስተባበል በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 144 የተደነገጉትን ሁኔታዎች ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ኑዛዜ የእኔን ልጅነት ለማሰረዝ የሚችል አይደለም የዚህ አይነት ይዘት የለውም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካቾች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካቾች ለሥር ፍርድ ቤት ባቀረቡት የፍርድ መቃወሚያም ሆነ በሰበር አቤቱታቸው የተጠሪ ወላጅ እናት ወ/ሮ አድማስወርቅ ጥላሁን ከሚች አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ ጋር የጋብቻ ግንኙነት አልነበራቸውም፡፡ ተጠሪ የተወለደው የሁለቱ ጋብቻ ከፈረሰ በኋላ ነው የሚል መቃወሚያ አላቀረቡም፡፡ አመልካቾች ተጠሪ የተወለደው አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ ለትምህርት አሜሪካ ሄደው ባለበት ጊዜ ነው በማለት አጥብቀው የሚያቀርቡትን ክርክር አግባብነት ካለው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ በአንድ ወንድና አንዲት ሴት መካከል ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ የተወለደ ልጅ አባቱ ነው የሚባለው ባልዬው እንደሆነ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 126 ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ተጠሪ የተወለደው በእናቱ ወ/ሮ አድማስወርቅ ጥላሁንና በአቶ ዘውዴ በሱፈቃድ መካከል

የነበረው ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ መሆኑ ያልተካደ በመሆኑ የተጠሪ አባት አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ መሆናቸውን ህጉ ግምት የያዘበት ጉዳይ ነው።

ተጠሪ በህግ ግምት የአቶ ዘውዴ በሱፈቃድ ልጅ መሆኑን ከማስረዳቱም በላይ አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ ባለቤታቸውን ሊጠይቁ ለእረፍት በመጡበት ጊዜ የተረገዘ መሆኑን የአቶ ዘውዴ በሱፈቃድ የቅርብ ዘመዶች በምስክርነት በማቅረብ አስረድተዋል። ይኸ በመሆኑ ተጠሪ የአቶ ዘውዴ በሱፈቃድ ልጅ አለመሆኑን ማስረዳት የሚቻለው በቤተሰብ ህጉ አንቀፅ 144 መሠረት ሳይሆን በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 167 መሠረት የመካድ ክስ በማቅረብና በቤተሠብ ህጉ አንቀፅ 168 እስከ አንቀፅ 173 ከተዘረዘሩት አንደኛውን ለማስረዳት የሚችል በቂ ማስረጃ በማቅረብ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የመካድ ክስ ለማቅረብ የሚችለው አባት ነህ ተብሎ በህግ ግምት የተሰጠው እሱ የሞተ እንደሆነ ተወላጆቹ እና ሌሎች ዘመዶቹ በቅደም ተከተል እንደሆነ የቤተሰብ ህጉ ደንግጓል። አንደኛ አመልካች ዘውዴ እሱባለው ሚስትና የሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ አመልካቾች እናት ብትሆንም በዚህ ጉዳይ ተጠሪ ላይ የመካድ ክስ የማቅረብ መብትና ችሎታ የላትም። ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎች ያቀረቡት መቃወሚያና መቃወሚያቸውን ለማስረዳት ያቀረቡት ማስረጃ ታዓማኒነት የሌለው መሆኑና የተጠሪ ማስረጃ ሚዛን የሚደፋ መሆኑ ፍሬጉዳይ የመመዘን ስልጣን ያላቸው የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተስማምተውበታል። ሚች አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ አደረጉት የተባለው ኑዛዜም ተጠሪ የሚች ልጅ ላለመሆኑ ብቃት ያለው ማስረጃ ተደርጎ እንዲወሰድ የሚያስገድድ ህግ የሌለ በመሆኑ በዚህ በኩል የበታች ፍርድ ቤቶች የህግ ስህተት ፈፅመዋል የሚል መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ ሆኖ አላገኘነውም። በአጠቃላይ የአመልካቾች ተጠሪ የሚች ዘውዴ በሱፈቃድ ልጅ አይደለም የሚለውን ክርክራቸውን የቤተሰብ ህጉ በሚደነግገው መሠረት በበቂ ሁኔታ አላስረዱም በማለት የበታች ፍርድ

ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ህጉን መሠረት ያደረገና ስህተት የሌለበት ሆኖ ስላገኘነው በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት አፅንተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. አመልካቾችና ተጠሪ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይኸ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰበር መ/ቁ/ 41857

ጥቅምት 24 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አሕመድ ሑሴን - ጠበቃ ማርቆስ ወ/ሰንበት ቀረበ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ የኔዓለም ተመስገን - ጠበቃ ደምሰው ዘገየ ቀረበ

2. ወ/ሮ የኔነሽ ሙሉጌታ ቀረበች

3. ወ/ሮ አስቱር ሙሉጌታ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የውርስ ሃብት ክፍፍልን መሠረት ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ 1ኛ ተጠሪ ናት፡፡ ክስ የመሠረተችው በአሁኑ አመልካች፣ በ2ኛ እና በ3ኛ ተጠሪዎች ላይ ነው፡፡ በክስዋም ሞግዚት የሆነችለት የኋላእሸት ሙሉጌታ የተባለውን ልጅ የውርስ መብት ለማስከበር ክሱን እንደመሠረተች ገልጻ ያለሞግዚት አድራጊዋ ስምምነት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር ያደረጉት የቤት ሺያጭ ውል እንዲፈርስ እና የቤቱ 1/3ኛ ለሞግዚት አድራጊዋ እንዲሰጥ ይወሰንላት ዘንድ ጠይቃለች፡፡

2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ለክሱ በሰጡት መልስ የቤቱ ግማሽ የሌላ ሰው መሆኑን በአንድ በኩል ሲገለጹ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ቀሪውን (የቤቱን ግማሽ) ለሦስቱ ተከፋፍሎ ከሣሽ ሞግዚት የሆነችለት ልጅ ድርሻውን 1/3ኛ ሊወስድ ይችላል ብለዋል፡፡ አመልካች

ግን ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል የሚል መቃወሚያ ከማቅረቡም በላይ፤ ቤቱን የገዛው ስመሃብቱ ለ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ከዞረ በኋላ እንደሆነና ከውሉ በኋላም ስመሃብቱ ለሱ መዛወሩን በመግለጽ ተከራክሮአል። ክሱን ያስተናገደው ፍ/ቤትም የሁሉን ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ፣ በአመልካች እና በ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ፈርሶአል። የቤቱ ግማሽ ከተቻለ በአይነት፣ ካልተቻለ ተሸጦ 1/3ኛ ለከሣሽ ሞግዚት አድራጊ ይሰጥ በማለት ወስኖአል።

በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ በዚህ ደረጃም ክርክሩ ተሰምቶአል። በመጨረሻም ፍ/ቤቱ ውሉ ይፈርሳል የሚለውን የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ሲያፀና 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በቤት ሽያጭ ውል ስም የወሰዱት ብር 100,000 ግን ከነወለዱ ለአመልካች ይመልሱ በማለት ወስኖአል። የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው።

እኛም አመልካች ህዳር 25 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል። ክርክሩ የተሰማው የቤት ሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ መደረጉ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው።

ከሥር ጀምሮ በተደረገው ክርክር እንደተመለከተው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት 1ኛ ተጠሪ ሞግዚት ለሆነችለት ልጅ እና ለ2ኛና3ኛ ተጠሪዎች በውርስ የተሰጠ ሃብት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ውርሱ ከመከፋፈሉ በፊት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ለአመልካች ሸጠውታል። የ1ኛ ተጠሪ ክርክር የተመሠረተውም የ3ቱም የጋራ የሆነው ንብረት ለመሸጥ የሁሉም የጋራ ባለሃብቶች ስምምነት ሊኖር ይገባል በሚለው ላይ ነው። በእርግጥም የጋራ የሆነውን ንብረት ለመሸጥ፣ ለማስተላለፍ ወይም በዋስትና ለማስያዝ ወይም የተመደበበትን አገልግሎት ለመለወጥ የጋራ ባለንብረቶቹ ሁሉ ስምምነት አስፈላጊ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕግ ቁ 1266 የተደነገገ ሲሆን፣ የውርስ ሃብትም

አካፋፈሉ እስኪፈጸም ድረስ በወራሾቹ መካከል ውርሱ ሳይነጣጠል እንደሚቆይ በፍ/ብ/ሕግ ቁ 1060(1) ተመልክቶአል፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ቤቱን ለአመልካች የሸጡት ስመሃብቱን በራሳቸው ካዛወሩ በኋላ ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የሺያጭ ውሉ ከመደረጉ ወይም ቤቱን ለአመልካች ከማስተላለፋቸው በፊት ከሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል የባለቤትነት የምስክር ወረቀት በስማቸው አግኝተው ነበር ማለት ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕግ ቁ 1195(1) እንደተመለከተው የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብትነትን በማወቅ በአስተዳደር ክፍል የባለሃብትነት የምስክር ወረቀት በተሰጠ ጊዜ የምስክር ወረቀቱን ያገኘው ሰው የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ባለሃብት ሁኖ ይቆጠራል፡፡ እንግዲህ በያዝነው ጉዳይ በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠውን ሁኔታ ከሕጉ ጋር አገናዝበን ስንመለከተው ቤቱ ያልተከፋፈለ የውርስ ሃብት መሆኑ ቀርቶ የ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የግል ሃብት እንደሆነ እንደሚቆጠር ነው መገንዘብ የሚቻለው፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ አመልካች ቤቱን የገዛው የሸያጮቹን የባለሃብትነት የምስክር ወረቀት በማየት ሲሆን፣ ይህን በመከተልም ቤቱ በራሱ ስም አዙሮ የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ያገኘበት በመሆኑ በአመልካቹ እና በ2ኛና 3ኛ ተጠሪዎች መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል የሚፈርስበት በሕግ የሚደገፍ ምክንያት የለም፡፡

ሌላው ቀጥለን የተመለከትነው 1ኛ ተጠሪ ሞግዚት የሆነችለት ልጅ ድርሻ እንዴት ይታያል የሚለው ነው፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በውሉ መፍረስ በመስማማቱ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በቤት ሽያጭ ስም የተቀበሉት ገንዘብ ለአመልካች እንዲመልሱ ወስኖአል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ 1ኛ ተጠሪ ሞግዚት የሆነችለት ልጅም ከሌሎቹ ወራሾች ጋር በመሆን ከቤቱ ድርሻውን ሊያገኝ ስለሚችል ችግር አይኖርም፡፡ በዚህ ሰበር ችሎት እምነት ግን ውሉ ሊፈርስ ስለማይገባ ቤቱ በወራሾቹ መካከል ይከፋፈል የሚል አካሄድ አይኖርም፡፡ ወራሾቹ ሊከፋፈሉ የሚችሉት ከቤቱ ሽያጭ

የተገኘውን ገንዘብ ነው። 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ቤቱን የእነሱ ሃብት ብቻ እንደሆነ አድርገው ቢሸጡትም፤ በመጨረሻ የታመነው ግን የ3ቱም ወራሾች ሃብት መሆኑ ስለሆነ ከዚህ ሃብት የተገኘው የሺያጭ ገንዘብም የ3ቱ ወራሾች ነው ማለት ነው። በመሆኑም 1ኛ ተጠሪ ሞግዚት የሆነችለት ልጅ የተለየ ሥነ-ሥርዓት መከተል ሳያስፈልገው ከቤቱ ሽያጭ ከተገኘው ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) ድርሻውን 1/3ኛ (አንድ ሦስተኛ) የማግኘት መብት አለው። በዚህ መሠረትም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል።

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 07153 ግንቦት 28 ቀን 99 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 57214 ጥቅምት 26 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348(1) መሠረት ተሻሽለዋል።
2. በአመልካች እና በ2ኛና 3ኛ ተጠሪዎች መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል አይፈርስም ብለናል።
3. 1ኛ ተጠሪ ሞግዚት የሆነችለት ልጅ ከቤቱ ሽያጭ ከተገኘው ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) ድርሻውን 1/3 (አንድ ሦስተኛ) 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ይስጡት ብለናል።
4. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ።
5. በዚህ ሰበር ችሎት ውሳኔ መሠረት ይፈጸም ዘንድ ለሥር ፍ/ቤቶች ይጻፍ። መዝገቡ ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ራ/ታ

የሠበር መ/ቁ 42361

ጥቅምት 05 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- ወ/ሪት ትዕግስት ንጉሴ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ኤስ.ኦ.ኤስ.ኢንፋንት ኢትዮጵያ - ነ/ፈጅ አያንቱ ግርማ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሠራተኛ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ የአሁኗ አመልካች ተጠሪ በሕገወጥ መንገድ የስራ ውሉን አቋርጧል በማለት የመሰረቱት ክስ ከታየ በኋላ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ እርምጃው ሕገወጥ በመሆኑ አመልካችን ወደ ስራ እንዲመልሳቸው በመ/ቁ 38316 ከወሰነላቸው በኋላ አመልካች ወደ ስራ ቢመለሱ ከተጠሪ ጋር መልካም የሥራ ግንኙነት እንደማይኖራቸው ገልፀው ለሕገወጥ ስንብት የሚከፈሉ ክፍያዎችንና የፕሮቪደንት ፈንድ እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ በማለት የአፈፃጸም ማመልከቻ አቅርበው ፍርድ ቤቱም የካሳ፣ ስንብትና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ትዕዛዝ ሠጥቶ የፕሮቪደንትና ክፍያ ለዘገየበት ክፍያን ግን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘትም አመልካች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች ታህሣስ 24 ቀን 2001 ዓ.ም በዓፉት 4(አራት) ገፅ የሠበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል። አቤቱታቸው ተመርምሮም የፕሮቪደንት ፈንድ ጥያቄያቸው ውድቅ የተደረገው ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሠበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል። ተጠሪም በተደረገለት ጥሪ መሠረት ቀርቦ ግንቦት 27 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገፅ ማመልከቻ መልሱን ሠጥቷል።

እኛም የግራ ቀኙን ክርክር የሠበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል።

ከክርክሩ መገንዘብ የተቻለው አመልካች በስር ፍርድ ቤት በመሰረቱት ዋና ክስ ላይ የፕሮቪደንት ፈንድ ጥያቄ ማንሳታቸውን ተጠሪ ደግሞ በድርጅቱ ውስጥ ፕሮቪደንት ፈንድ ያለመኖሩንና ከሠራተኛው ደመወዝ ላይ ለፕሮቪደንት ፈንድ የተቆረጠ ምንም ገንዘብ ያለመኖሩን በመግለፅ መከራከሩን ነው። በዚህ በግራ ቀኙ ክርክር ማስረጃ ተመርምሮ ተገቢው ዳኝነት አልተሠጠበትም፤ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ የአሳረፈው የስራ ውል መቋረጡ ሕገ ወጥ በመሆኑ ላይ ሲሆን የሠጠውም መፍትሔም (Relief) አመልካች ወደ ስራቸው እንዲመለሱ የሚል የነበረ መሆኑንም ተረድተናል። አመልካች በፍርድ ቤቱ ውሣኔ መሠረት ወደ ስራ መመለሱን በመተው በምትኩ የተለየዩ ክፍያዎች ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ የአፈፃፀም ማመልከቻ አቅርበዋል።

በመሠረቱ ወደ ስራ እንዲመለስ የሚል ውሣኔ ያገኘ ሠራተኛ ከዚህ ውሣኔ በኋላም ቢሆን ወደ ስራ ለመመለስ ፍላጎት ከሌለው ካሣ ተከፍሎት ከስራ እንዲሰናበት በማድረግ የሥራ ክርክሩን የሚወስነው አካል ሊወሰን እንደሚችል አዋጅ ቁጥር 377/96 በአንቀጽ 43(3) ስር አስቀምጧል። ይህ ሊሆን የሚችለውም ቀድሞ የተወሰነ ውሣኔ ከመፈጸሙ በፊት ነው።

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ወደ ስራ ሊመለሱ ይገባል ተብሎ የተወሰነው ውሣኔ ከመፈፀሙ በፊት በምትኩ የተለያዩ ክፍያዎች ተከፍለውኝ ልሰናበት የሚል የአፈፃፀም ማመልከቻ ማቅረባቸው ግራ ቀኙን ያከራከረ ነጥብ አይደለም፡፡ አከራካሪው ነጥብ የፕሮቪደንት ክፍያ ሲሆን የስር ፍርድ ቤቶች ጥያቄውን ያልተቀበሉት ወደ ስራ የመመለስ አማራጭ ቀርቶ በአዋጁ አንቀፅ 43/3/ መሰረት በካሳ ሠራተኛው እንዲሰናበት ሲደረግ በአፈፃፀም ሊጠየቅ የሚችለው በዋናው የፍሬ ነገር ክርክር ውሳኔ ያላገኘ ክፍያ አይደለም በሚል ነው፡፡ በእርግጥ በአፈፃፀም ሊጠየቅ የሚገባው ውሳኔ ያረፈበት ጉዳይ ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓቱ ከቁጥር 371 ጀምሮ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ሆኖም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43(3) ስር የተመለከተው ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ በግልፅ ዳኝነት ተጠይቆበት ውሳኔ ሳይሰጥ ከተጠየቁት ዳኝነቶች መካከል ወደ ስራ የመመለስ ጥያቄ ላይ ብቻ ውሳኔ ከተሠጠ እና ሰራተኛው ወደ ስራ መመለስ ሳይፈልግ ሲቀር ቀድሞ ዳኝነት በጠየቀባቸው ነገር ግን ውሳኔ ባላረፈባቸው ነጥቦች ላይ ዳኝነት ሊጠይቅ እንደሚችል ያስረዳል፡፡ ይሁን እንጂ ጥያቄው ሲቀርብ በግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች የቀረበ ማስረጃ በተገቢው መንገድ ታይቶ ሊወሰን የሚገባው ነው፡፡ የአመልካች የፕሮቪደንት ፈንድ ጥያቄ በተጠሪ በኩል ክርክር የቀረበበት ነው፡፡ ወደ ስራ እንዲመለስ ለተወሰነለት ሰራተኛ የፕሮቪደንት ፈንድ እንዲከፈል የሚወሰንበት የሕግ አግባብም የለም፡፡ እንዲሁም የፕሮቪደንት ፈንድ እንደሌሎች ከአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት የሚመነጩ የመብት ጠያቄዎች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162 ስር በተመለከቱት የይርጋ ጊዜ ገደቦች የሚታገድ ሳይሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1845 ድንጋጌ ስር በተመለከተው የአስር ዓመት የጊዜ ገደብ የሚታገድ ስለመሆኑ ይህ ችሎት በሠ/መ/ቁ 32545 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሠጥቶበታል፡፡ በመሆኑም አመልካች የፕሮቪደንት ክፍያ ጥያቄ በአፈፃፀም መዝገብ ሳይሆን ሌላ የዋና ክርክር መዝገብ

ከፍተው ተገቢ ክርክር ተደርጎበት ውሳኔ የሚሰጥበት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 42459 ግንቦት 28 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠው ትዕዛዝ እና በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 68296 መስከረም 10 ቀን 2001 ዓ.ም የተሠጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ 42594

ጥቅምት 10 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሀይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- አቶ ኑሩ ሠይድ - በሌሉበት

ተጠሪ፡- አፍሪካዊት ሕንጻ ተቋራጭ - ነ/ፈጅ ዮሴፍ ገ/እግዚአብሔር

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የሥራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በደቡብ ወሎ ዞን በኮምበልቻ ወረዳ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ከመጋቢት 1 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ በተከሳሽ ድርጅት በቋሚ ሠራተኛነት ተቀጥሬ በመሥራት ላይ እያለሁ በ21/2/2001 ዓ.ም ማስጠንቀቂያ ሳይደርሰኝና ሥራውም ሳይጠናቀቅ የሥራ ውሉን ከሕግ ውጭ አቋርጧል፡፡

ስለሆነም ወደ ሥራዬ እንድመለስ ይህ ካልሆነም ልዩ ልዩ ክፍያዎች ተፈጽመውልኝ ልሰናበት በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተከሳሽም በበኩሉ በሰጠው መልስ የተከሳሽ መ/ቤት የሥራ ባህሪይ የኮንስትራክሽን ሥራ በመሆኑንና ለዚህም ሥራው ሲያልቅ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የመቀነስ መብት ያለው ሲሆን ከሳሽም የተቀጠሩበት ሥራ በመጠናቀቁ ደመወዝ፣ የትርፍ ሰዓት ክፍያና ያልተጠቀሙበት የዓመት ዕረፍት በገንዘብ ተለውጦ ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ የተደረገ ስለሆነ ክሱ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበላትም የወረዳው ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ሰምቶ ተከሳሽ ሥራው በመጠናቀቁ ምክንያት ከሳሽን ከሥራ ስለማሰናበቱ አላስረዳም፡፡ ስለዚህ ከሳሽ ከሥራ ከታገዱበት ጊዜ ጀምሮ ያልተከፈለ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ሥራ እንዲመለሱ ተከሳሽ ይህንን ለመፈጸም ፈቃደኛ ካልሆነ የስራ ስንብት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያና ክፍያ የዘገየበትን እንዲከፍል በማለት ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

ተከሳሽ በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት ይግባኙን ሠርዟል፡፡

ለዚህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ችሎቱ አቤቱታውን መርምሮ ስንብቱ ሕገወጥ ነው መባሉ በሰበር ሊታይ እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን ጠርቷል፡፡ ሆኖም ተጠሪ የቃል ክርክር ለመስማት በተቀጠረበት ቀን መጥሪያ ደርሷቸው ስላልቀረቡ ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ሠጥቷል፡፡

የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን በበኩላችንም ጉዳዩን ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ መርምረነዋል፡፡

በአሰሪና ሠራተኛ መካከል የሚደረግ የሥራ ውል ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ የሕግ ግምት እንደሚወሰድ ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 9 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህን የሕግ ግምት ማፍረስ የሚቻለውም በአንቀጽ 10 ላይ እንደተመለከተው የሥራ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ሥራ የተደረገ መሆኑን በማስረዳት ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የሥራ ውል ለተወሰነ ሥራ የተደረገ ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የኮምቦልቻ ወረዳ ፍ/ቤት ስንብቱ ሕገወጥ ነው ያለው የተወሰነው ሥራ የተጠናቀቀ መሆኑን አመልካች አላስረዳም በሚል ነው፡፡ ሆኖም ግን ከፍርዱ ግልባጭ በግልጽ መገንዘብ እንደሚቻለው የተወሰነው ሥራ እየተገባደደ

በመሄዱ ምክንያት አመልካች የሥራ ውሉን ያቋረጠ መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ ከሥራ የተሰናበቱት የተቀጠሩበት የተወሰነ ሥራ በመጠናቀቁ ወይንም እየተጠናቀቀ መሆኑ ከተረጋገጠ በአዋጁ አንቀጽ 24(1) ላይ እንደተመለከተው የሥራ ስንብቱ በሕግ በተደነገገው መሠረት እንደተቋረጠ የሚያሰገነዝብ ነው፡፡ ስለሆነም ስንብቱ ሕጋዊ መሆኑን መገንዘብ የተቻለ ስለሆነ የሥር ፍ/ቤቶች ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት ተጠሪ ወደ ሥራ እንዲመለሱ ወይንም የተለያዩ ክፍያዎች ተፈጽሞላቸው ይሰናበቱ በማለት የሰጡት ውሳኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የኮምቦልቻ ወረዳ ፍ/ቤት ታህሳስ 10 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንደዚሁም የደቡብ ወሎ ዞን ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 24604 ታህሳስ 24 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ከሥራ የተሰናበቱት በሕጉ አግባብ ስለሆነ ወደ ሥራ ሊመለሱም ሆነ የተለየዩ ክፍያዎች ሊፈጽምላቸው አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰበር መ/ቁ 42682

ጥቅምት 10 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ ፋንታነሽ ሲሳይ ሙላቴ ቀረቡ

2. አለሙ ደምሴ

3. ወ/ሪት ትእግስት ደምሴ

ተጠሪ፡- ሞላ ደምሴ ቀረበ ጠበቃ ፋንታ አየለ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ ልጅነትን ለማረጋገጥ በቀረበው ጥያቄ ላይ ተመስርቶ የተካሄደውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው ተጠሪ ቀደም ሲል ለፍ/ቤት ባቀረበው ጥያቄ መሠረት የሚች ደምሴ ፀጋዬ ልጅ መሆኑ ተረጋግጦ ተወስኖ ነበር፡፡ አመልካቾች ክርክሩ ውስጥ የገቡት ውሳኔውን በመቃወም እንዲሻርላቸው በመጠየቃቸው ነው፡፡ ተቃውሞአቸውም ተጠሪ የሚች ልጅ አይደለም የሚል ስለነበር፤ መቃወሚያው የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪን በማስቀረብ የግራ ቀኝ ወገኖቹን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም በተጠሪ በኩል የቀረበው የሰው እና የሰነድ ማስረጃ በእርግጥም የሚች ልጅ እንደሆነ አረጋግጦአል፡፡ ተቃዋሚዎች ይህን ማስረጃ ማስተባበል አልቻሉም በማለት የቀድሞው ውሳኔውን አፅንቶአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በበኩሉ ክርክሩን ከሰማ በኋላ ተጠሪ የሚች ልጅ ነው በማለት ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካቾች ጥር 12 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፉት ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተፈጽሞአል የሚሉትን ስህተት በመግለጽ ውሳኔው ይሻርላቸው ዘንድ ጠይቀዋል። በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል። ክርክሩ የተሰማው ተጠሪ የሚች ልጅ ነው በሚል የተሰጠው ውሳኔ ከተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 143 አንፃር ሲታይ አግባብነት ያለው ነው ወይስ የለውም? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው። በመሆኑም በዚህ ረገድ የተሰማው የግራቀኝ ወገኖች ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመለክተናል።

ከላይ እንደተገለጸው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ግራቀኝ ወገኖችን ያከራከረው የልጅነት ጥያቄ በተመለከተ ማስረጃዎችን ሰምቶአል። በሰማው ማስረጃም ሚች (አባት ነው የተባለው ሰው) ተጠሪን እንደልጁ በማድረግ ሲንከባከብ እንደነበር፣ ትምህርት ቤት ወስዶ እንዳስመዘገበው፣ ከቤተሰቶቹ ጋር በመቀላቀል ያኖረው እንደነበር ማረጋገጡን በውሳኔው ላይ አመልክቶአል። በሌላ በኩል ደግሞ አመልካቾች በተጠሪ በኩል የተሰማውን ማስረጃ ሊያስተባብሉ እንዳልቻሉ በትችቱ ገልጾአል። በመጨረሻም በማስረጃ ያረጋገጠው ፍሬ ነገር በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ (አዋጅ ቁ 213/92) አንቀጽ 143(ሠ) መሠረት አባትነትን ለማረጋገጥ በቂ ምክንያት እንደሆነ በመገንዘቡ ተጠሪ የሚች ልጅ ነው በማለት እንደወሰነ ተገንዝበናል። አመልካቾችም ቢሆኑ እየተከራከሩ ያሉት የሥር ፍ/ቤት አረጋግጫለሁ ያለውን ፍሬ ነገር አላረጋገጠም በማለት ሳይሆን፣ ተጠሪ ተወልጃለሁ የሚለው ከጋብቻ ውጪ በተፈጸመ የግብረስጋ ግንኙነት በመሆኑ ይህንኑ ግንኙነት በማያጠራጥር ሁኔታ ማስረዳት ሲገባው አላስረዳም በማለት እንደሆነ ከአጠቃላይ የክርክራቸው ይዘት ለመገንዘብ ችለናል።

የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 143 “በፍርድ ስለሚነገር አባትነት” በተመለከተ ዝርዝር ድንጋጌዎችን ይዞአል። እነዚህም ከንኡስ አንቀጽ(ሀ) እስከ (ሠ)

ድረስ ያሉት ሲሆኑ፣ አመልካቾች በመከራከሪያነት ያነሱት ነጥብ በንኡስ አንቀጽ (መ) በተመለከተው ድንጋጌ ላይ የተመሠረተ ነው። ይህ ድንጋጌ የልጁ እናትና አባት የተባለው ሰው በሕግ የታወቀ ግንኙነት ባይኖራቸውም፤ በሕግ በተመለከተው የእርግዝና ጊዜ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ በግብረ ሥጋ ግንኙነት አብረው የኖሩ መሆናቸው ከተረጋገጠ አባትነትን በፍርድ ውሳኔ ሊታወቅ እንደሚችል ስለሚያመለክት እንደሌሎቹ ድንጋጌዎች አንደኛው አባትነትን በፍርድ ውሳኔ የማወቂያ ዘዴ (ሁኔታ) ነው። ይህ ማለት ግን በዚህ ድንጋጌ የተመለከተው ሁኔታ ባለመረጋገጡ ብቻ አባትነትን በፍርድ ውሳኔ ማወቅ አይቻልም ማለት አይደለም። በተጠቀሰው አንቀጽ 143 መሠረት አባትነትን በፍርድ ውሳኔ ማወቅ የሚቻለው ከንኡስ አንቀጽ (ሀ) እስከ (ሠ) ካሉት ድንጋጌዎች ውስጥ በአንዱ የተመለተው ሁኔታ ሲሟላ ነው። በመሆኑም ቀጣይነት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ስለመኖሩ ተጠሪ በማስረጃ አላረጋገጠም የሚለው የአመልካቾች ክርክር ተቀባይነት የለውም። ስናጠቃልለው የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪ የሚች ልጅ በማለት በሰጡት ውሳኔ የተፈጸመ የሕግ ስህተት የለም ለማለት ችለናል።

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 27622 ጥቅምት 1 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 63272 ህዳር 4 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348(1) መሠረት አፅንተናል።
2. ተጠሪ የሚች ልጅ ነው መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል።
3. ግራቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ።

መዝገቡ ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ራ/ታ

የሰበር መ/ቁ 42749

ጥቅምት 24 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን - ሃና ግዛው ቀረበች

ተጠሪዎች፡- 1. ስዩም አብርሃ ቀረበ

2. አየለ ዝቅአርጌ ቀረበ

3. መስፍን እንዳዘነው ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 69613 ታሕሣሥ 16 ቀን 2001 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ ላይ ነው፡፡ ጉዳዩ በአሠሪና ሠራተኛ መካከል የተነሳውን የሥራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ተጠሪዎች በአመልካች ላይ ክስ የመሠረቱት የሥራ ውላችን ከሕግ አግባብ ውጪ የተቋረጠ በመሆኑ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎን ወደሥራችን እንመለስ ዘንድ ይወሰንልን በማለት ነው፡፡ አመልካችም በበኩሉ ለክሱ በሰጠው መልስ ተጠሪዎች የተቀጠሩት በወቅቱ የነበረውን የሥራ ብዛት ለማቃለል ለተወሰነ ጊዜ ነው፡፡ የሥራው መብዛት በመቃለሉም ተሰናብተዋል፡፡ ይህም ሕግን የተከተለ አሠራር ነው በማለት ተከራክሮአል፡፡ ክሱን ያስተናገደው ፍ/ቤት ክርክሩን ከመረመረ በኋላ ተጠሪዎች የተቀጠሩት ለተወሰነ ጊዜ መሆኑን በማስረጃ አረጋግጫለሁ በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪዎች ውሳኔውን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ

ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረባቸው ክርክሩ በድጋሚ የተሰማ ሲሆን፣ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው በማለት በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮአል። የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው።

የሰበር ችሎቱም አመልካች ጥር 14 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት ተጠሪዎችን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቶአል። አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ አግባብ ውጪ ነው በማለት የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ነው። በመሆኑም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ ተመልክተናል።

ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር ይዘት ማየት እንደቻልነው ተጠሪዎች የተቀጠሩት አመልካች በወቅቱ አጋጥሞት የነበረው የሥራ መብዛት ለማቃለል በሚል እንደሆነ በማስረጃ ተረጋግጦአል። በዚህ ረገድ በፍሬ ነገር የተረጋገጠው እውነታ በሁለቱም የሥር ፍ/ቤቶች ግንዛቤ አግኝቶአል። የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ አግባብ ውጪ ነው ለማለት የቻለው የተቀጠርነው ላልተወሰነ ጊዜ ነው በማለት ተጠሪዎች ያቀረቡትን ክርክር በመቀበል ወይም የተቀጠሩበት ሥራ አላለቀም በማለት ሳይሆን፣ ተጠሪዎች በውላቸው ከተመለከተው ጊዜ በተጨማሪ ለ45 ቀናት ሠርተዋል የሚል ምክንያት በመስጠት ነው። በበኩላችን እንደምናየው ፍ/ቤቱ የተከተለው አካሄድ ትክክል ነው የሚባል አይደለም።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ተጠሪዎች የተቀጠሩት በወቅቱ የነበረውን የሥራ መብዛት እግምት ውስጥ ገብቶ ነው። አመልካች የሥራ ውሉን ባቋረጠ ጊዜም ሥራው አልቆ እንደነበረ ተረጋግጦአል። በመሆኑም ውሉ የተቋረጠው በሕግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም ለሚለው አከራካሪው የሕግ ጭብጥ መልስ መስጠት የሚቻለው በፍሬ ነገር

ረገድ የተረጋገጠውን እውነታ በማየት ነው የሚሆነው፡፡ በፍሬ ነገር የተረጋገጠው ተጠሪዎች የተቀጠሩበት ሥራ መጠናቀቁ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ተጠሪዎች የሠሩበት ጊዜ ማጠር ወይም መርዘም በዚህ ላይ የሚያመጣው ለውጥ የለም፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ 377/96 አንቀጽ 10(1)(ሐ) እንደተመለከተው የሥራ መብዛት በሚኖርበት ጊዜ ሥራን ለማቃለል በሚል የሚደረገው የሥራ ውል ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሥራ ከሚደረጉት ውሎች አንዱ ነው፡፡ ውሉ የሚቋረጠውም በውሉ የተመለከተው ሥራ ወይም ጊዜ ሲያበቃ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪዎች የተቀጠሩበት ሥራ አልቆአል፡፡ በመሆኑም ውሉ መቋረጡ የግድ ነው፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ይህን ሁኔታ ያላገናዘበ በመሆኑ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ የሆነ ስህተት ያለበት ነው፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 69613 ታሕሣሥ 16 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348(1) መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 12617 ሰኔ 4 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ፀንቶአል፡፡
3. በአመልካች እና በተጠሪዎች መካከል የነበረው የሥራ ውል የተቋረጠው በሕግ አግባብ ነው ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ 42766

ጥቅምት 10 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሀይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካቾች፡- እነ ወ/ት ሠናይት ኃ/ማርያም - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አበበች ወርቁ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ በአመልካቾች አባት እና በተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ መፈረስን ተከትሎ የንብረት ክፍፍልን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌደራል መ/ደ/ፍ/ቤት የውርስ አጣሪ ሰይሞ አጣሪውም ጉዳዩን ከተመለከተ በኋላ ለሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነውን የቤ.ቁ 084 ጨምሮ የባልና ሚስቱ የጋራ ሀብት ነው በማለት ሪፖርቱን ለፌደራል መ/ደ/ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም ይህንኑ ሪፖርት ተቀብሎ ማጽደቁን ተገንዝቦአል፡፡

ከዚህ በኋላም የአሁን አመልካቾች የቤ.ቁ 084 የሆነው ቤት የሚች አባታችን የግል ንብረት ሆኖ ሳለ የባልና ሚስቱ የጋራ ንብረት ነው ተብሎ በውርስ አጣሪ የተደረሰበትን ሪፖርት የፌደራል መ/ደ/ፍ/ቤት ተቀብሎ ሪፖርቱን ማጽናቱ በአግባቡ አይደለም በማለት የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌደራል ከ/ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የውርስ አጣሪው ቤቱ የጋራ ነው ወደሚል ድምዳሜ የደረሰው የጋብቻ ውሉን መሠረት በማድረግ ሲሆን ነገር ግን ውሉ የጋራ ያደረገው የቤቱን ገቢ እንጂ ቤቱን እንዳልሆነ ከውሉ በግልጽ መረዳት ይቻላል ካለ በኋላ የሥር

ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር ይሄው ቤት የአመልካቾች አባት የግል ሀብት ነው በማለት ውሳኔ መስጠቱን መዝገቡ ያስረዳል፡፡

የአሁን ተጠሪም በከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ይግባኝ ባይና የመ/ሰጭዎች አባት ሲጋቡ የቤ.ቁ 084 አስቀድሞ በሚች ተሰርቶ የነበረና ሁለት ክፍል ቤት ብቻ የነበረ ሲሆን ነገር ግን በጋብቻ ላይ እያሉ ቤቱን በተደጋጋሚ ማደሳቸው ይህ ቤት እንዳይሸጥ በማሰብም ሌላ ቤት ሸጠው ለዕዳ መክፈያነት በማዋል ቤቱ ከመሸጥ ስለማዳናቸው ቤቱም በፊት ከነበረው ሁለት ክፍል ላይ ተጨማሪ 9 ክፍል ሰርቪስ ቤቶችን በጋራ ስለመስራታቸውና አስቀድሞ ቤቱ የሚገኝበት ይዞታ 300 ሜ.ካሬ ብቻ የነበረ ሲሆን ነገር ግን በተጨማሪ ግንባታ ሲደረግ ይዞታውም ወደ 578 ካ.ሜትር ከፍ ስለማለቱ በክርክሩ የተረጋገጠ ስለሆነ በዚህ ሁኔታ ቤቱ የመ/ሰጪዎች አባት የግል ንብረት ነው መባሉ በአግባቡ አይደለም በማለት በመሻር የባልና ሚስቱ የጋራ ሀብት ነው ሲል ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ለሰበር ሊቀርብ ይገባል ብሎ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ ክርክር ያስነሳው ቤት የባልና ሚስቱ የጋራ ሀብት ነው? ወይንስ የባል የግል ንብረት የሚለው ነው፡፡

ከዚሁ ጭብጥ አኳያም ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበራቸው ንብረቶች የግል ንብረቶቻቸው ሆነው እንደሚቀሩ በተሻሻለ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 57 ላይ ተመልክቷል፡፡ የአመልካቾች አባትና ተጠሪ ጋብቻቸውን በፈጸሙ ጊዜ የቤ.ቁ 084 በሚች የአመልካቾች አባት ስም ተመዝግቦ ሁለት ክፍል ቤት ብቻ እንደነበር የተረጋገጠ ሲሆን ይህ ፍሬ

ነገርም ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ ሆኖም ግን ግራ ቀኙ ሚያዝያ 13 ቀን 1966 ዓ.ም ያደረጉት የጋብቻ ውል ክርክር የተነሳበትን ቤትም ሆነ ሌሎች በባል ስም ተመዝግበው የሚገኙ ንብረቶችን የጋራ ለማድረግ እንደተስማሙ ከውሉ አጠቃላይ ይዘት መገንዘብ የሚቻል ከመሆኑም በላይ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ እንደተመለከተው ባልና ሚስቱ ጋብቻቸው ጸንቶ በቆየበት ጊዜ ቤቱን በተደጋጋሚ ማደሳቸው፣ በንግድ ምክንያት የመጣና በጋራ የሚፈለግባቸውን የግብር ክፍያ በተመለከተም ይሄው ቤት እንዳይሸጥ በማሰብ ሌላ ንብረት ሸጠው የግብር ዕዳውን በመክፈል ቤቱን ማቆየታቸውና ቀድሞ የነበረውንም ይዞታ በማስፋፋት ሌላ ተጨማሪ 9/ዘጠኝ/ ክፍል ሰርቪስ ቤቶች ስለመስራታቸው የተረጋገጠ እንደመሆኑ መጠን ይህም ቀድሞውንም ቢሆን በጋብቻ ውሉ ቤቱን የጋራ ለማድረግ የነበራቸውን ሃሳብ የሚያጠናክር ነው፡፡

ስለሆነም ግራ ቀኙ ባደረጉት የጋብቻ ውል አከራካሪው ቤት የጋራ እንዲሆን የተስማሙ ከመሆኑም ሌላ ጋብቻው ጸንቶ በቆየ ጊዜም የቤቱ አገልግሎት በመሠረታዊነት የተለወጠ ስለሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር ቤቱ የባልና ሚስቱ የጋራ ሀብት ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 31335 ታህሳስ 27 ቀን 2001 ዓ.ም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር የሰጠው ፍርድ በአግባቡ ስለሆነ ጸንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳሆናች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰበር መ/ቁ 43248
ጥቅምት 10 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
ሐጐስ ወልዱ
ሂሩት መለሰ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሃና ተፈራ ጉግሳ - ሄኖክ ተፈራ (ወኪል) ቀረበ
ተጠሪዎች፡- 1. የልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 14 ጽ/ቤት - አትርሳው መሸሻ
2. ወ/ሮ ሂሩት አለምረው

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ ከሕግ አግባብ ወጪ የተያዘው ቤት ይለቀቅልኝ በሚል የቀረበውን ክስ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ አመልካች ከአባትዋ በውርስ የተላለፈልኝ ነው የምትለውን በልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 14 ክልል ውስጥ የሚገኘው በቁጥር 068 የሚታወቀው ቤት ለቀው ያስረክቡአት ዘንድ በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሠረተች ሲሆን፣ ተጠሪዎችም ለክሱ በሰጡት መልስ ቤቱ ከ1968 ዓ.ም ጀምሮ ተወርሶ በመንግስት ባለሃብትነት እንደሚተዳደር በመግለጽ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የስረ-ነገር ክርክር አቅርበዋል፡፡ ክሱን የሰማው ፍ/ቤትም የተከሣሾችን ክርክር በመቀበል ክሱን ውድቅ አድርጎአል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የሰማው የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትም በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ አፅንቶአል፡፡ በመጨረሻም አመልካች ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት

ሰበር ችሎት አቤቱታ አቅርባ የነበረ ሲሆን ችሎቱ የተፈጸመ የሕግ ስህተት የለም በማለት አቤቱታውን ውድቅ አድርጎአል። የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው።

አመልካች ጥር 25 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈችው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተፈጽሞአል የምትለውን ስህተት በመግለጽ አቤቱታዋን አቅርባለች። በበኩላችንም ይህን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል። ክርክሩ የተሰማው የአከራካሪው ቤት ማነው (የአመልካች አባት ወይስ መንግስት) የሚል ክርክር በተነሳበት ጉዳይ ላይ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ነበራቸው ወይስ አልነበራቸውም? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው።

ከፍ ሲል እንደተገለጸው ክርክሩ የቤት ባለቤትነት ጥያቄን መሠረት ያደረገ ነው። አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት ባለሃብት መሆንዋን በመግለጽ ቤቱ እንዲለቀቅላት ስትጠይቅ፤ ተጠሪዎች ደግሞ ቤቱ ተወርሶአል። የመንግስት ሃብትም ሆኖአል የሚል መከራከሪያ አቅርበዋል። በመሆኑም በዚህ ረገድ ውሳኔ ሊያገኝ የሚገባው ጭብጥ የአከራካሪው ቤት ባለቤት (ባለሃብት) ማነው? የሚል ነው። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች የቤት ባለሃብትነትን መሠረት አድርጎ የቀረበውን ክስ ለማየት የዳኝነት ስልጣን ነበራቸው ወይ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ የቻለውም በዚህ ምክንያት ነው።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን በዝርዝር ተመልክቶ የሚገኘው በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41 ነው። በዚህ ድንጋጌ መሠረት በፍ/ቤቶቹ የዳኝነት ስልጣን ስር ከሚወድቁት ጉዳዮች አንዱ የተከተማው አስተዳደር ከሚያስተዳድራቸው የመንግስት ቤቶች ጋር በተያያዘ የሚነሱትን ክርክሮች የሚመለከት እንደሆነ በዚሁ አንቀጽ 41(1)ረ

ተመልክቶአል፡፡ ይህ የሰበር ችሎት ለዚህ ድንጋጌ ቀደም ሲል በሰበር መ.ቁ 32376 በሰጠው ውሳኔ ትርጉም ሰጥቶአል፡፡ በዚህም ችሎቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች ድንጋጌውን መሠረት በማድረግ የሚያዩአቸው ጉዳዮች ከባለቤትነት (ከቤቱ ባለሃብትነት) መብት በመለስ የሚነሱትን ክርክሮች ብቻ የሚመለከቱ ናቸው ብሎአል፡፡ እንግዲህ የሰበር ችሎቱ የሰጠውን ትርጉም መሠረት አድርገን በዚህ መዝገብ የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ለማየት የዳኝነት ሥልጣን አልነበራቸውም መደምደሚያ ነው የምንደርሰው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በከተማው አስተዳደር ፍ/ቤቶች በመታየት ላይ የነበሩና በአዋጅ ቁ 361/95 መሠረት በከተማው ፍ/ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ሥር የማይወድቁ ጉዳዮች በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማው ፍ/ቤት መታየታቸው እንደሚቀጥል ቻርተሩን (አዋጅ ቁ.361/95ን) እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁ.408/96 አንቀጽ 2(3) መደንገጉን ተመልክተናል፡፡

አመልካች ክሱን ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረበችው ህዳር 3 ቀን 96 ዓ.ም ሲሆን አዋጅ ቁ.408/96 ፀንቶ ሥራ ላይ የዋለው ከሰኔ 8 ቀን 96 ዓ.ም ጀምሮ ነው፡፡ ፍ/ቤቱ ሲያከራክር ቆይቶ ውሳኔ የሰጠው ደግሞ የካቲት 6 ቀን 98 ዓ.ም ነው፡፡ ይህ ማለትም ጉዳዩ በመታየት ላይ ስለነበረ ፍ/ቤቱ በአዋጅ ቁ.408/96 በአንቀጽ 2(3) በተደነገገው መሠረት ሥልጣን ነበረው በማለት ነው፡፡ በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ፍ/ቤቶች ሥልጣን ሳይኖራቸው ነው ጉዳዩን ያስተናገዱት ለማለት የሚያስችል ምክንያት የለም፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 00949 የካቲት 6 ቀን 98 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ.ቁ 03196

መጋቢት 9 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ 06740 ታሕሣሥ 10 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348(1) መሠረት ፀንተዋል፡፡

2. አመልካች ያቀረበችው የሰበር አቤቱታ አልተቀበልንም፡፡
3. ግራቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸው ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመጣው ቁ.ልደ/00949/567/96 የሆነው መዝገብ ወደመጣበት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰበር መ/ቁ 43271

ጥቅምት 24 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካቾች፡- የአቶ ታሪኩ ዓለሙ ወራሾች - ጠበቃ ግርማ አይታገድ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ - ወንድወሰን ጥሩነህ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፀናው ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ጉዳዩ ከቤት ኪራይ ውል ጋር ተያይዞ የተነሣውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ሲሆን፣ ክሱን የመሠረተው በአመልካቾች አውራሽ ላይ ነው፡፡ ክሱም የአመልካቾች አውራሽ አቶ ታሪኩ አለሙ የፋርማሲ ንግድ ሥራ ለማካሄድ በውል በተከራየው ቤት ላይ ሕገወጥ ግንባታ ስለጨመረበት ውሉ ፈርሶ ቤቱን እንዲመልስ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ ተከሣሹም ለክሱ በሰጠው መልስ ተጨማሪ ግንባታ ማካሄዱን በማመን እና በሌላ በኩል ደግሞ ግንባታውን ያካሄደው የክፍሉ ቀበሌ (ቀበሌ 10) ጽ/ቤት በሰጠው ፈቃድ መሠረት መሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ ይደረግለት ዘንድ ጠይቆአል፡፡ አመልካቾች ክርክሩ ውስጥ የገቡት ተከሣሹ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ስለሞተ በወራሽነት መብታቸው በክርክሩ ለመቀጠል ነው፡፡ ፍ/ቤቱ ግን ከከሣሽ ጋር የቤት ኪራይ ውል የላችሁም የሚል ምክንያት በመስጠት እና የተከሣሹን መሞት

መሠረት በማድረግ ውሉን አፍርሶአል። ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በበኩሉ ክርክሩን የሰማ ሲሆን፣ በመጨረሻም በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ አፅንቶአል።

አመልካቾች ጥር 1 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፉት ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተፈጸመ የሚሉትን መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመግለጽ አቤቱታ አቅርበዋል። በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል። በመቀጠልም አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ አግባብነት ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል።

ከሥር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር በዝርዝር እንዳየነው የአመልካቾች አውራሽ/አባት ለክሱ መልስ ሰጥተው የነበረ ቢሆንም፤ ክርክሩ ከመጠናቀቁ /ከውሳኔ/ በፊት መሞታቸው፣ አመልካቾች የሚች ልጆችና ወራሾች ስለመሆናቸው አከራካሪ አለመሆኑ፣ ይህን መሠረት በማድረግም አመልካቾች በአባታቸው ምትክ ተከሣሾች ሆነው በክርክሩ እንዲቀጥሉ እንዲፈቀድላቸው መጠየቃቸው፣ ፍ/ቤቱ ግን ከከሣሽ ጋር የኪራይ ውል ግንኙነት የላችሁም የሚል ምክንያት በመስጠት ጥያቄአቸውን ውድቅ ማድረጉን፣ በቤቱ ላይ ክርክር የማቅረብ መብት የላችሁም የሚል ተጨማሪ ምክንያትም መስጠቱ በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጦአል።

እንደምንመለከተው ክርክሩ የፍትሐብሔር ጉዳይን የሚመለከት በመሆኑ ሊመራ የሚገባው አግባብነት ባላቸው የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ነው። እንደሚታወቀው የክርክር ሂደት የራሱ የሆነ የተወሰነ ጊዜ ስለሚያስፈልገው ክርክሩ ከመጠናቀቁ በፊት ከሣሽ ወይም ተከሣሽ የሚሞቱበት አጋጣሚ ሊኖር ይችላል። የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉም ይህን ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ "ስለተከራካሪዎቹ ወገኖች መሞት ወይም መክሰር" በሚለው በሁለተኛ መጽሐፍ በምዕራፍ 2 ስር

ድንጋጌዎችን አስቀምጦአል። በዚህ መዝገብ ለተያዘው ጉዳይ በቀጥታ አግባብነት ያለው በቁጥር 50 የተመለከተው ድንጋጌ ሲሆን፣ ይህም ተከሣሹ አንድ ብቻ ሆኖ እሱም የሞተ እንደሆነ፣ የክሱ ሃላፊነት ነዋሪ ሆኖ የሚቆይ ሲሆንና አግባብ ያለው ወገን ማመልከቻ ሲያቀርብ የሚቹ ንብረት አስተዳዳሪ ተተክቶ ክርክሩን ይቀጥል ዘንድ ትዕዛዝ መስጠት እንደሚቻል ይገልጻል። ከዚህም በተጨማሪ በሚቹ እግር ተተክቶ ተከሣሽ እንዲሆን የተደረገው ሰው በሕጉ መሠረት ለክሱ የመከላከያ ክርክሩን ማቅረብ እንዳለበት ደንግጎአል።

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ አመልካቾች የሚች ልጆችና ወራሾች እንደመሆናቸው አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የውል አጣሪዎች ናቸው። በዚህም የውርስ ሃብት የሆነውን ንብረት አስተዳዳሪዎችም ናቸው። ሚች ከተጠሪ የተከራዩት ቤቱ ቢሆንም፤ በቤቱ ውስጥ ሲካሄድ የቆየው ግን የፋርማሲ ንግድ ሥራ ነው። የንግድ ሥራው ባለቤት ሚች በመሆናቸውም የንግድ መደብሩ የውርስ ሃብት ሆኖ ነው የሚቆጠረው። በመሆኑም ንግዱ የሚካሄድበትን ቤት በተመለከተ የተደረገው የኪራይ ውል ሊቋረጥ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለው ጭብጥ ሊወሰን የሚችለው አመልካቾች በአውራሻቸው እግር ተተክተው ከሚያቀርቡት መከላከያ አንጻር ታይቶ ነው። በሕጉ እንደተመለከተው አመልካቾች ለክርክሩ አግባብ ያላቸው ወገኖች በመሆናቸው በቤቱ ላይ ክርክር የማቅረብ መብት የላችሁም የሚባሉ አይደሉም። አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ ከዚህ አኳያ ሲታይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ነው የተገኘው።

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 75150 ግንቦት 25 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 68586 ሕዳር 8 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካቾችን በሚች እግር ተተክተው ክርክሩ ውስጥ እንዲገቡ በማድረግ እና የሚያቀርቡትን የመከላከያ ክርክር በመስማት የመሰለውን ውሣኔ ይስጥ በማለት ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 341 መሠረት ይመለስለት ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰበር መ/ቁ 43417

ጥቅምት 3 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ
ሐጐስ ወልዱ
ሂሩት መለሰ
ታፈሰ ይርጋ
አልማው ወሌ

አመልካች፡- የአዲስ አበባ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ
ጠበቃ ኅበና እጅጉ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ባይነሳኝ ፀጋዬ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ያለአግባብ ተይዞአል የተባለውን ቤት ይለቀቅ ዘንድ የቀረበውን ክስ መነሻ በማድረግ የተካሄደውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረችው አመልካች ቤተ ክርስቲያን ስትሆን፣ በተጠሪ ላይ ክስ የመሠረተችው በአራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 11 ውስጥ የሚገኘው ቤት ከመሠረቱ የቤተክርስቲያንዋ ንብረት እንደሆነ በመግለጽ ተጠሪ ቤቱን ለቆ እንዲያስረክባት፣ ቤቱን እንዲለቅ ማስጠንቀቂያ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ላለው ጊዜም በወር ብር 200 ኪራይ እንዲከፍል እንዲወሰንለት ጠይቃለች፡፡ ተጠሪም በበኩሉ በሰጠው መልስ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የስረ ነገር ክርክር አቅርቦአል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ ከሣሽ ያቀረበችው ካርታ በኢትዮጵያ ወንጌላዊት ማህበር ስም የተሰጠ እንጂ የከሣሽን ስም የማይጠቅስ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት እና የመክሰስ መብት የላትም በማለት ክሱን ሰርዞአል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ አፅንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች የካቲት 5 ቀን 2001 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል። አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች ያቀረበችው ክስ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 33(2) አንፃር ታይቶ ውድቅ የተደረገበትን አግባብ ለመመርመር ነው። በመሆኑም ይህ በጭብጥነት የተያዘው ነጥብ ከግራቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል።

ቀደም ሲል እንደተመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችን ክስ የሰረዘው ወደጉዳዩ ስረ-ነገር ገብቶ ክርክር ሳይሰማ ነው። ለዚህ የሰጠው ምክንያትም አመልካች በአስረጅነት ያቀረበችው የቦታ (ቤት) ይዞታ ካርታ የስዋን ስም አያመለክትም የሚል ብቻ ነው። አመልካች እየተከራከረች ያለችው ደግሞ "የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ማህበር" በሚል ይታወቅ የነበረው ስያሜ ከብዙ ዓመተት በፊት "የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ" በሚል ተተክቶአል። የቀድሞ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ማህበር ማለት እኔ ነኝ። ይህም በሰዎች ምስክርነት አስረዳለሁ በማለት ነው። ፍ/ቤቱ ግን አመልካች ከጅምሩ ለመከሰስ የሚያስችል መብት ያላት ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረበችም እሚል መደምደሚያ ላይ በመድረሱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 33(2)ን በመጥቀስ ክሱን ውድቅ ከማድረግ አልፎ በአመልካች የተቆጠሩትን ማስረጃዎች አልሰማም።

በበኩላችን እንደምናየው አመልካች በቤቱ ላይ አለኝ የምትለውን መብት እና የስዋንም ማንነት ለማስረዳት ያስችለኛል የምትለውን ማስረጃ አግባብ ካለው የሥነ ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌ መሠረት እስካቀረበች ድረስ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 33(2)ትን በመጥቀስ ክሱ የሚሰረዝበት ምክንያት የለም። በሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሠረት የቀረቡ የሰውም ሆነ የሰነድ ማስረጃዎች ልዩነት ሳይደረግባቸው ሊሰሙ ይገባል። አመልካች እና ተጠሪ በቤቱ ላይ ያላቸው መብት በንፅፅር ሊታወቅ (ሊረጋገጥ) የሚችለውም ክርክሩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.241 እና ተከታዮቹ ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት በአግባቡ ሲሰማ

እና ጭብጡም በማስረጃ ሲነጥር ነው። ተጠሪ ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረበው ክርክር ጭምር እንዳመለከተው በቤቱ ላይ የባለሃብትነት መብት አለኝ አይልም። ዋናው የመከራከሪያ ነጥቡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክሱን ለመሠረዝ የጠቀሰው ምክንያት ነው።

ነገሩን አጠቃለን ስንመለከተው የሥር ፍ/ቤቶች የአመልካችን ክስ የሰረዙት በሥነ-ሥርዓት ሕጉ የተቀመጠውን የክርክር እና ማስረጃ መስማት ሂደት ሳያከናውኑ ነው። በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል።

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 37138 መጋቢት 29 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 67893 ህዳር 10 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348(1) መሠረት ተሽረዋል።
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ያቀረበችው ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 33(2) መሠረት ሊዘጋ የማይገባው መሆኑን ተገንዝቦ ክሱን እንዲሰማ። ግራ ቀኝ ወገኖች የሚያቀርቡትን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላም የመሰለውን ውሳኔ ይሰጥ ዘንድ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 341 መሠረት ይመለስለት ብለናል።
3. በዚህ ሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ። መዝገቡ ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ራ/ታ

የሰበር መ/ቁ 43614

ጥቅምት 12 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. መንበረፀሃይ ታደሰ

2. ሂሩት መለሰ

3. ታፈሰ ይርጋ

4. አልማው ወሌ

5. ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የምስራቅ ቀጠና ጉምሩክ - ነ/ፈጅ ደስታ ተስፋው ቀረበ

ተጠሪ፡- ሊሻን ይርጉ - አልቀረበም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው ተጠሪ በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ ተጠሪ በክሳቸው አመልካች መኪናዬን ከጥቅም ውጪ ስላደረገ ቀደም ሲል ከስሼው አደጋው ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ በቀን ብር 50 (ሃምሳ ብር) ታስቦ ከፍሎኛል፡፡ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ውሳኔ እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ ስላልተከፈለኝ በቀን 50 ብር ታስቦ ብር 139,050.00 (አንድ መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ሃምሳ ብር) ይክፈለኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በወር ብር 25 (ሃያ አምስት) ታስቦ ብር 43,650 አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ የነበረ ቢሆንም ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም አሁን ክስ የቀረበበት ከቀድሞ ክስ ጋር ተጠቃሎ ሊቀርብ የሚገባው መሆን አለመሆኑን ከፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 216 አኳያ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙም ቀርበው ክርክራቸውን

በፀሁፍ አቅርበዋል። ችሎቱም አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ ከተያዘው ጭብጥ አኳያ መርምሯል።

ተጠሪ ቀደም ሲል በመኪናቸው ላይ ለደረሰው አደጋ አመልካችን ሲከሱ የመኪናቸውን ግምት እና ጉዳቱ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ ያለውን የተቋረጠ ጥቅም ጠይቀዋል። በዚሁ መሰረትም ውሳኔ አግኝተዋል። አሁን አዲስ ባቀረቡት ክስም ቀደም ሲል ላቀረቡት ክስ ምክንያት በሆነው አደጋ ሳቢያ ክስ ካቀረቡበት ጊዜ ጀምሮ ውሳኔ እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ ለተቋረጠ ጥቅም ኪሳራ እንዲከፈላቸው ነው የጠየቁት። አመልካች በበኩሉ ይህ የዳኝነት ጥያቄ ቀደም ሲል ካቀረቡት ክስ ጋር ተጠቃሎ ሊቀርብ የሚገባውና ተነጥሎ የቀረ ስለሆነ በድጋሚ ክስ ሊቀርብበት እንደማይገባ ተከራክሯል። በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 216(3)(4) ስር አንድ ከሳሽ ሊከስበት ሲችል ሆነ ብሎ ባስቀረው ሃብት ምክንያት ወይም ደግሞ የሚጠይቀው ዳኝነት ከአንድ በላይ ሆኖ ፍ/ቤቱን ሳያስፈቅድ ራሱ ቀንሶ ያስቀረውን መብት እንደገና ሌላ ክስ ማቅረብ የተከለከለ መሆኑ ተመልክቷል። በአንድ ክስ ተጠቃለው ዳኝነት ሊጠየቅባቸው የሚችሉ ጉዳዮች ተነጣጥለው ብዙ ክስ በማቅረብ በየፍርድ ቤቶች ክርክር እንዳይበዛ እንዲሁም ተከሳሹ በአንድ ክስ ሊከላከለው የሚችለውን ጉዳይ የተነጣጠለ ክስ በማቅረብ እንዳይጉላላ ለማድረግ ሲባል ተጠቃለው በአንድነት እንዲቀርቡ ህጉ ያዛል።

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ቀደም ሲል ክስ ሲያቀርቡ መኪናው ላይ አደጋ በመድረሱ ምክንያት አደጋው ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ የተቋረጠ ገቢ እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል። ጉዳቱ ክሱ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ ሊቀጥል እንደሚችል መገመት አስቸጋሪ አይሆንም። በእርግጥ ክሱ ውሳኔ ሊያገኝ የሚችልበት የጊዜ እርዝመት ከወዲሁ መገመት ሊያስቸግር ይችል ይሆናል። ነገር ግን ክሱ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ ጉዳቱ ሊቀጥል እንደሚችል እስከታወቀ ድረስ ጊዜውን ገምቶ ዳኝነት በመክፈል ካሳ እንዲከፈል መጠየቅ የማይቻልበት ሁኔታ አይኖርም። ምናልባት

ትክክለኛው የገንዘብ መጠን ስለማይታወቅ ሙሉ ዳኝነት መክፈል አስቸጋሪ ቢሆን እንኳን ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በወሰነ ጊዜ ቀሪው የዳኝነት ገንዘብ እንዲከፈል ሊያደርግ ስለሚችል ከፊሉ የካሳ ጥያቄ ተነጥሎ ክስ ሊቀርብ የሚገባበት ምንም አይነት የህግ አግባብ አይኖርም፡፡ ተጠሪ ለዚህ ሰበር ችሎት በሰጡት መልስ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ውሳኔ እስካገኘበት ጊዜ ድረስ ያለው የተቋረጠ ጥቅም ሆነ ብለው ቀንሰው ያስቀሩ ሳይሆን ፍ/ቤቱ ይወስነዋል በሚል ግምት መሆኑን መግለፃቸው ይኸው የዳኝነት ጥያቄ በቀድሞ ክስ ሊወሰን ይችል የነበረ መሆኑን ያውቁ እንደነበር የሚያመለክት ነው፡፡ በመሆኑም በቀድሞ ክስ አጠቃለው ሊጠይቁ ሲገባ ነጥለው ባስቀሩት ሃብት ላይ ድጋሚ ክስ ማቅረብ የማይችሉ ሆኖ ሳለ የስር ፍ/ቤቶች ይህን የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌ ወደጎን በመተው የጉዳት ካሳው እንዲከፈል መወሰናቸው መሰረታዊ የሥነ-ሥርዓት ህግ ስህተት መፈፀማቸውን ያሳያል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ፍ/ቤት በመ/ቁ 23573 ሐምሌ 24 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 04079 የካቲት 4 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪ የጠየቁት ዳኝነት ቀድሞ ካቀረቡት ክስ ጋር ተጠቃሎ ሊቀርብ ይገባው የነበረ በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 216(3) ዳግም ክስ ሊያቀርቡበት አይችሉም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰበር መ/ቁ 44203
ጥቅምት 24 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ
ሐጐስ ወልዱ
ሂሩት መለሰ
ታፈሰ ይርጋ
አልማው ወሌ

አመልካች፡- ቶማ ዳቂታ
ተጠሪ፡- አዋሳ እርሻ ልማት ድርጅት

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሠሪና ሠራተኛ መካከል የተነሣውን የስራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበረው አመልካች ነው፡፡ በተጠሪው ላይ ክስ የመሠረተው የሥራ ውሌ ከሕግ ውጪ ተቋርጦብኛል በማለት ሲሆን፣ ተጠሪ ደግሞ ለክሱ በሰጠው መልስ የሥራ ውሉ ሊቋረጥ የቻለው ከሣሽ (የአሁኑ አመልካች) በጥበቃ ሥራ ላይ ተመድቦ በመሥራት ላይ ሳለ የሥራ ግዴታውን ባለመወጣት ግምታቸው ብር 3000.00 የሆነ ልዩ ልዩ የመለዋወጫ ዕቃዎችን ግብረአበር አዘጋጅቶ ሰርቆ ሲወስድ ስለተገኘ ነው በማለት ተከራክሮአል፡፡ ክሱን ያስተናገደው የሃዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የሁለቱን ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው እሚል ድምዳሜ ላይ ደርሶአል፡፡ በመቀጠልም አመልካች ያልተከፈለው ደመወዝ ተከፍሎት ወደስራው ይመለስ፣ ተጠሪ ወደሥራው አልመልስም ካለም የሥራውል ከሕግ ውጪ ሲቋረጥ የሚከፈሉትን ክፍያዎች በሙሉ ይክፈል በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የሃዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን የሰረዘ ሲሆን፣ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ግን በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት የለውም

የሚል ምክንያት በመስጠት ሽሮታል። በዚህም የሥራ ውሉ የተቋረጠው በሕጉ መሠረት ነው በማለት ወስኖአል። የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው።

እኛም አመልካች የካቲት 26 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል። አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የሥራ ውሉ የተቋረጠው በሕግ አግባብ ነው በሚል የተሰጠውን ውሳኔ ለመመርመር ተብሎ ነው። በመሆኑም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል።

ከፍ ሲል እንደተገለጸው ተጠሪ የሥራ ውሉን አቋረጥኩ የሚለው አመልካች ፈጸመ የተባለውን ጥፋት መሠረት በማድረግ ነው። ክሱን የሰማው ፍ/ቤትም ይህን ለማስረዳት ተብለው በተጠሪ የተቆጠሩትን ምስክሮች ሰምቶአል። ምስክሮቹ በሰጡት ቃል አመልካች በጥበቃ ሥራ ላይ በነበረበት ጊዜ በተጠሪ የተጠቀሱትን የመለዋወጫ ዕቃዎች ተሸመ ጫኔ የሚባለው ሰው በሚገፋው የእንጨት ጋር አስጭኖ ከድርጅቱ (ተጠሪ) ግቢ ሰውሮ በማውጣት ላይ እንዳለ እጅ ከፍንጅ መያዙን እንደተነገረ ፍ/ቤቱ በውሳኔው ላይ አስፍሮአል። ከዚህ በኋላ የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው በማለት ሊወሰን የቻለው አመልካች "በተጠሪ ንብረት ላይ የስርቆት ወይም የመሸሸግ ወንጀል ፈጽሞአል" ለማለት ከጥርጣሬ በላይ ምስክሮች ስላላስረዱ የሚል ምክንያት በመስጠት እንደሆነም ከውሳኔው ሐተታ ላይ ለማረጋገጥ ችለናል። የክልሉ የሰበር ችሎት በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ከሕግ ውጪ ነው ለማለት የበቃው ውሳኔው በምስክሮች በግልጽ የተረጋገጠውን ሃቅ እንዳልተረጋገጠ በማድረግ የተሰጠ ነው በማለት ነው።

በበኩላችንም እንደምናየው ተጠሪ ባስያዘው ጭብጥ ላይ የተሰሙት ምስክሮች እንደክርክሩ በሚገባ አስረድተዋል። ተጠሪ ከዚህ በላይ እንዲያስረዳም አይጠበቅበትም

በሌላም በኩል ተጠሪ ያስማው ማስረጃም በአመልካች አልተስባበለም ወይም ተቃራኒ ማስረጃ አልቀረበበትም ምስክሮች የሰጡት ቃል አመልካች ከተጠሪ ፈቃድ ሳያገኝ ንብረቶችን ደብቆ /ሰርቆ/ ሲወስድ ስለመያዙ በሚገባ የሚያረጋገጥ በመሆኑ ድርጊቱ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ 377/96 አንቀጽ 14/2/ መሰረት ሕገወጥ ነው፡፡ በአዋጅ አንቀጽ 27/1/ መ/ እንደተመለከተውም ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውል ለማቋረጥ በቂ ምክንያት ነው፡፡ አመልካች ፈጸመ ስላተባለው ድርጊት የተረጋገጠው ፍሬ ነገር ከሕጉ ጋር በሚገባ ተስማምቶ እያለ ፍርድ ሰጭው አካል ይህን ሁኔታ እንዳላ00000የ ሆና የሚያልፍበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ከዚህ የተነሳም የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት እና ጉዳዩን በይግባኝ ያየው ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መባሉና መሻሩ ተገቢ ነው፡፡ ስለዚህም አቤቱታ የቀረበበት የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ ትክክል ነው ብለናል፡፡

ው ሳ ኔ፣

1. አቤቱታ የቀረበበት በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 26337 የካቲት 25 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቶአል፡፡
2. በአመልካችና እና በተጠሪ መካከል የነበረው የስራ ውል የተቋረጠው ከሕግ አግባብ ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ወ/ነ

የሰ/መ/ቁ 44449

ጥቅምት 24 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ሚሊኒየም የሳኔተሪና የቢንቢ ሥራ ማሕበር ወኪል ጌታሁን ስዩም ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ወርቁ አበቡ ቀረቡ

መዝገቡን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በአዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሣሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ ጥቅምት 04 ቀን 2001 ዓ.ም. በዛፋት ክሰ ከአመልካች ማሕበር ጋር በክልሉ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱትሪ ኤጀንሲ አማካኝነት በሕጋዊ መንገድ ተደራጅተው በስራ አስኪያጅነት ለአንድ አመት የመሩ መሆኑን፣ከገንዘብ ጥቅም ያላንዳች ምክንያት ተከልክለው ያለጥፋት ከማሕበሩ በጥቂት ግለሠቦች ፍላጎት መባረራቸውን፣ የቀረባቸው ጥቅም ብር 1180.00 ተከፍሏቸው ወደ አባልነት እንዲመለሱ ለአደራጆች አመለክተው ቢወሰንላቸውም በመመሪያው መሠረት ሊመልሷቸው አለመቻሉን በመዘረዝር እርምጃው ደንቡን የጣሰ መሆኑ ታይቶ ጠቅላላ አባላት ጉባኤ ውሣኔ ተሠርዞ ከእነሙሉ መብትና ጥቅም ጋር ወደ አባልነት እንዲመለሱ ይወሠንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ አመልካችም ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የሌለው መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ሲያነሳ በፍሬ ነገር ረገድም የማሕበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የማሕበሩን ሊቀመንበር የመምረጥ ወይም የማንሳት፣ አንድን ሠው የማሕበሩ አባል እንዲሆን ማድረግ ወይም ከአባልነት እንዲሠናበት የመወሠን ሥልጣን በመተዳዳሪያ ደንቡ መደንገጉን፣እርምጃው የተወሰደውም ተጠሪው ለማሕበሩ ጥቅም ቅድሚያ በመስጠት ኃላፊነታቸውን ባግባቡ ሊወጡ ባለመቻላቸውና ተመክረውና ይቅርታ ጠይቀው ከተመለሱ በኃላም ያልታረሙ መሆኑን ብር 1000.00 በአቴንዳንሱ

በሠሩት መሠረት የተቀነሰ መሆኑንና ብር 180.00 ያላግባብ ያወጡት የማሕበሩ ገንዘብ ስለመሆኑ ዘርዝሮ ክሱን ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል የሥር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ማስረጃዎችን መርምሮ አመልካች ተጠሪን ከማሕበሩ አባልነት እንዲሠናበት ያደረገው አላግባብ መሆኑን በምክንያትነት ይዞ የማሕበሩ አባላት ጉባኤ ውሣኔን በመሠረዝ ተጠሪ የማሕበሩ አባል እንዲሆኑ፣ ብር 1800.00 እንዲከፈላቸው እና መብታቸው ካሉት አባላት ጋር እኩል እንዲታይ፣ ከአባልነት አላግባብ በመሰናበታቸው የቀረባቸው ጥቅማ ጥቅም ቢኖር ታስቦ እንዲከፈላቸው በማለት ወስኗል። በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለአዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሠርዞበታል። ጉዳዩ ለክልሉ ሠበር ችሎት ቀርቦም ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኃላ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል። የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ ለማስቀየር ነው።

የአመልካች ጠበቃ መጋቢት 11 ቀን 2001 ዓ.ም. በባፋት 3/ሶስት/ ገፅ የሠበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል። ይዘቱም ባጭሩ፡- የሥነ ሥርዓት ግድፈትና ጥሰት ያለበት፣ የማሕበሩን መተዳዳሪያ ደንብ ይዘትን ያላገናዘበ ስለመሆኑ በመዘርዘር የስር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው። የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ለሠበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ቀርበው ሐምሌ 28 ቀን 2001 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ አቅርበዋል። ይዘቱም ባጭሩ፡- የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት በክልሉ አዋጅ ቁጥር 104/1999 እና በደንብ ቁጥር 21/1996 መሠረት ሥልጣን እንዳለው፣ በፍሬ ነገር ረገድ የተሠጠው ውሣኔውም ማስረጃን መሠረት ያደረገ በመሆኑ ሊነቀፍ እንደማይገባው በመዘርዘር ውሣኔው ሊፀና ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሠበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካለቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል። እንደመረመረው ተጠሪ ወደ ማሕበሩ አባልነታቸው ይመለሱ ተብሉ የመወሠኑ አግባብነት ተገቢ መሆኑ ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል።

ከክርክሩ ሂደት መረዳት የተቻለው አመልካች በክልሉ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪ ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ እና በጥቃቅንና አነስተኛ ማሕበራት ማደራጃ ደንብ መሠረት የተቋቋመ ልዩ አቋም ያለው ራስ አገዝ ማሕበር መሆኑን ነው።

በመሠረቱ አመልካችን ዓይነት የሆኑን ማሕበራት የሚያስፈልጉት ተመሳሳይ ፍላጎት ባለቸው ሠዎች መካከል በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ሕብረት በመፍጠር ገንዘብን፣ዕውቀትን፣ንብረትንና ጉልበትን በማስተባበር ቁጠባንና እርስ በርስ መደጋገፍን መፍጠር መሆኑ ይታመናል። ከዚህ አስፈላጊነታቸው መረዳት የሚቻለው የአንድ ማሕበር አባላት ግንኙነት በፈቃደኝነትና መግባባት ላይ የተመሠረተ መሆን ያለበት መሆኑን ነው።። በማሕበሩ አባላት መካከል ሠላማዊ የሆነ ግንኙነት በሌለበት ሁኔታ ሥራውን በአንድ ላይ እንዲቀጥሉ ማድረግ ማሕበራቱ የተቋቋመበትን ዓላማ እንዳያሳኩ የሚያደርግ ነው። እያንዳንዱ ማሕበር የራሱ መተዳዳሪያ ደንብ የሚኖረው ሲሆን ስለማሕበሩ ሥራ አመራር ኮሚቴ አባላትና ሌሎች የሥራ ኃላፊዎችን ምርጫ፣ ሹመትና የሥራ ጊዜ እንዲሁም ከኃላፊነት ስለሚታገዱበት ወይም ስለሚወገዱት ሁኔታ በመተደዳሪያ ደንቡ ያስቀምጣል።

በተያዘው ጉዳይም አመልካች የራሱ የሆነ መተዳዳሪያ ደንብ ያለው ስለመሆኑ በመግለፅ ተከራክሯል። አመልካች በስር ፍርድ ቤት ጠቅሶ ባቀረባቸው የደንቡ ድንጋጌዎች ይዘት ላይ ተጠሪ መከራከሪያ የሌላቸው መሆኑን ከክርክሩ ሂደት ተረድተናል። ይህ ችሉትም ደንቡን ተመልክቶታል። እንደተመለከተውም መተዳዳሪያ ደንቡ የማህበሩ ደንቡ የማሕበሩን ዓላማ፣የአባልነት መመዘኛዎችን፣ስለጠቅላላው ጉባኤ ሥልጣልንና ተግባር፣የማሕበሩ ሊቀመንበር ተግባርና ኃላፊነት እና ሌሎች በርካታ ጉዳዩችን አካትቶ የያዘ ነው። ለዚህ ክርክር ቀጥተኛ አግባብነት ያለው የደንብ ክፍልም አንቀጽ 17.2፣ 18 እና 22 ናቸው። በእነዚህ ድንጋጌዎች መሠረት የማሕበሩ አባል ግዴታውን ካልተወጣ ጠቅላላ ጉባኤው ጉዳዩን መርምሮ ከአባልነት እንዲሠረዝ እንደሚያደርግ፣ በማሕበሩ ከፍተኛ ጉዳዩች ላይ የመጨረሻ ውሣኔ መስጠት እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል። ተጠሪ በጠቅላላው ጉባኤ ማሕበሩ አባልነት እንዲሠረዙ ተወስኗል። የሥር ፍርድ ቤትም ይህንኑ አረጋግጦ የአመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረገው ተጠሪ ከማሕበሩ አባልነት የተሠናበቱ ያለግባብ መሆኑን ከምስክሮች ቃለ ተገንዝቤአለሁ በማለት ነው። ይሁን እንጂ ይኸው የሥር ፍርድ ቤት ድምዳሜ የማሕበሩን ዓላማና ደንቡን ያላገናዘበ ነው። በመሆኑም ተጠሪ ከማሕበሩ የተሠናበቱት የማሕበሩ መተደዳሪያ

ደንብ በሚፈቅደው ሥርዓት በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በአዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በስራ ክርክር መዝገብ ቁጥር 16253 ሕዳር 07 ቀን 2001 ዓ.ም. ተሠጥቶ በአዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 5832 በቀን 06-05-2001 ዓ.ም. እንዲሁም በደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ችሎት በመ/ቁጥር 25333 በቀን 02-07-2001 ዓ.ም. የፀናው ውሣኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ከማሕበሩ አባልነት የተሠረዙ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/ሸ

□□□□ □/□ 44800
□□□□ 05 □□ 2002 □.□

□□□□- 1. □□□□□□□□ □□□
2. □□□ □□□
3. □□□ □□□
4. □□□□ □□
5. □□ □□□□

□□□□□□- □□ □□□□□□ □□□ - □/□□□□□ □□□□ □□□

□□□□- □□□□□□ □□□ □□□ - □/□□ □□□□ □□□□ □□□

□□□□ □□□□□ □□□□ □□□ □□□□□□□

□ □ □

□□□ □□□□ □□□□□ □□□□ □□ □□□□□□ □□□ □□□□ □□□□□ □□/□/□□□ □□□ □□ □□□□□ □□ □□□□ □□□□ □□□□□ □/□□/□□/□□□□ □□□□ □□ □□□□□ □□□ □□□□□ □□/□□□ □□□ □□□ 23 □□□ 12 □□□ □□□□□□ □□ □□□□ □□□□□□ □□□ □□ □□□ □□□□ □□□□ □□□□□ 2 □□□ □□□□ □□□□□□□ □□□□□ □□□□ □□□□ □□□□□□ □□□ □□□□ □□□□□□ □□□ □□□□ □□□□ □□□□□□□ □□□ □□□ □□□ □□□□ □□□ □□□□ □□ □□□□ □□□ □□□ □□□□□□□ □□□ □□□□ □□□□□□□ □□□□ □□□□□ □□ □□□ □□□□□□□□ □□□□□ □□□□ □□□□□□□ □□□□□ □□ □□□□□ 10 □□□ □□□□ □□□□ □□ □□□□□ □□□□ □□□ □□□ □□□□ □□□□ □□□□□□ □□□□□□ □□□□□□ □□□□□ □□□ □□□□□□□ □□□□□□ □□ □□ □□□□ □□□□ □□□□□□□□ □□□□ □□□□ □□□ □□ □□□□□□ □□□□□□□□ □□□□ □□□□□□□ □/□□□ □□ □□□ □□□□□ □□□ □□□□□ □□□□□ □□□ □□□□ □□□□□□□ □□□□□ □□/□/□ 3058(1) □□□□□□□ □10 □□□ □□ □□□□ □□□ □□□□ □□□□ □□ □□□□□□ □□□□ □□□□ □□ □□□□□□ □□□□ □□□□ □□□□□□ □□□ □□□ □□ □□□□□ □□/□□□□ □/□□ □□□□ □□□□ □□□□ □□□ □/□□ □□□

□□□□□□□□□□ □□□□□ □□□□□ □□□□□ □□□□□□ □□□□ □□□□ □□ □□□□□ □□□□□□□ □□□□ □□□□□ □□□□□□ □□ □□□□□□□ 10 □□□□ □□□□□□ □□/□/□ 3058(1) □□□□□ □□□□□ □□ □□ □□□□ □□□□□ □□ □□□□□ □□□□□ □□□□□□□□ □□□□ □□□□□□□ □□□□□□ □□□□□ □□□□ □□□□□□□ □□□□□□ □□ □□ □□□□□□□□ □□□□□ □□□□□□□□□ □□□□□ □□□□□□ □□□□□□□□□ □□□□□□□□

□□□□□□ □□□□□ □□□□□ □□□□□□ □□□□□ □/□□/□□/□□□□□ □□□□□□ □□□□ □□□□□□ □□□□□ □□□□□□□□ □□□□□ □□□□ □□□□□□□□ □1987 □.□ □□□□□ □□□□□□ □□□□□□ □□□□□ □□□□□ □□□□□ □□□□□□ □□□□ □□□□□□□ □□□□□ 24 □□ 1992 □.□ □□□□□□□□ □□□□□□ □□□□□□ □□□□□□□□ □□□□□□ □□□□□ □□ □□ □□□□□ □□□□□□□□ □□/□/□ 3058(1)□ □□□□□□ □□□□□ □□□□□□ □□□□ □□□□□ □□□□□□ □□□□□□□□□ □□□□□□ □□□□□□ □□ □□□□□□ □□□□□□□□□ □□□□□□□□

□□□□□□□□□ □□□□□ □□□□□ □□□□ □□□□ □□□□□□ □□□□□□□ □□ □□□□□ □□□□ □□□□ □□□□ □□□□ □□□□□

□□□ □□□□□ □□□□□ □□□□ □□□□□ □□ □□□□ □□□□□□ □□□□□ □□□□□□□□□ □□ □□□□□ □□□□ 10 □□□□ □□□□ □□□□□ □□□□□□ □□□□□ □□ □□□□□□ □□□□□ □□□□□□ □□□□□ □□□□□□ □□□□□□ □□□□ □□□□□□□ □□ □□□□□ □□□□ □□□□□ □□□□ □□□□□ □□ □□□□ □□□□ □□□□□ □□□□□□ 10 □□□□ □□□□□ □□□□ □□ □□□□□□□ □□□□ □□□□□ □□□□□□ □□□□ □□ □□□□□□ □□/□/□ 3058(2) □□□□□□□□□□□□ □□□□□□ □□ □□ □□□□□□ □□□□□□□ □□□□□ □□□□□ □□□□□□□□ □□□□ □□□□ □□□□ □□□□□ □□□□□□□ □□□□ □□□□ □□□□ □□□□□ □□□□□□ □□□□ □□□□ □□□□ □□□□□ □□□□ □□ □□□□□□ □□□□□□□□□ □□□□ □□□□- □□□□ □□□□□ □□□□□□ □□□□ □□□□ □□ □□□□□ □□ □□□□ □□□□ □□□□□ □□□□□ □□□□□ □□□□□ □□□□□□ □□□□□□□□□ □□□□ □□□□□□□ □□□□□ □□ □□□□□□ □□□□□ □□□□□□ □□ □□□□□ □□□□ □□□□□ □□□□□ □□□□□□ □□□□□ □□□□□□□ □□□□ □□□□□ □□□□ □□ □□□□□□ □□□□ □□□□□ □□ □□□□ □□□□ □□ □□□□□ □□□□□ □□ □□□□□ □□ □□□□□ □□□□□□ □□□□□□□ □□ □□□□□□□ □□□□□ □□□□□ □□□□□□□□ □□□□ □□□□ □□□□□ □□ □/□□ □□□□□□□ □□□□ □□□□□□□ □□□□□ □□□□ □□□□ □□□□□□ □□□□□□□□ □□/□/□ 3058(1) □□□□□□□□□□ □□□□□□ □□□□-□□□□

□□□□□□□□ □□□□□□□ □□□□□ □□□□□□□ □□□□ □□□□□□□□ □□□□ □□□□ □□□□ □□□□□□ □□□□ □□ (lapse) □□□□□□□□□□ □□□□ □□ □□□□ □□□□ □□ □□□□□ □□□□□ □□ □□□□□□ □□ □□□□ □□□□ □□□□□□□□□□ □□□□ □□□□□ □□□□□ □□ □□□□□□□ □□□□ 10 □□□□ □□□□ □□□□□□□ □□□□□□□ □□□□□□□ □□□□ □□□□□□ □□□□ □□□□□ □□□□□□ □□□□ □□□□□□ □□□□□□□ □□/□/□ 1632(2) □□□□□□□□□□ □□□□□□ □□□□ □□□□ 10 □□□□ □□□□□ □□□□□ □□□□□□□ □□□□ □□□□□□□ □□□□□□ □□□□ □□ □□□□□□□ □□□□ □□□□□□ □□ □□□□□□□ □□□□□□□

□□□□ □□□□ □□□□□ □□□□ 17 □□ 1987 □.□ □□□□□□□ □□□□ □□□□□ □□□□□□ □□ □□□□□□ □□ □□□□□□□□□□ □□□□ 12 □□ 1999 □.□ □□□□ □□□□□□□ □□□□□□ □□□□□ □□□□□□□ □□□□□□□ □□□□□ □□ □□□□□ □□□□□□ □□ □□□□□ □□ □□ □□ □□□□□□□□□□ □□□□ □□□□□ □□□□□ □□□□□□□ □□□□ □□□□□□ □□□□□ □□□□□□□ 10 □□□□ □□□□□ □□□□□ 24 □□ 1992 □.□ □□□□□□□□ □□□□□□□ □□□□□□ □□□□□ □□ □□□□□□ □□ □□□□□□□□□ □□□□□□ □□□□□□ □□□□□□□□ □□□□□□□ □□□□□ □□□□□□□□ □□□□□□□ □□□□□□□□ □□□□□□ □□□□□ □□□□ □□□□□ □□□□□□ □□□□ □□ □□□□ □□□□□□□□□ □□□□□ □□□□ □□□□□□ □□□□ □□□□□ □□ □□ □□□□□□□□□□□□ □□/□/□ 3058 □□ □□□□□□□ □□□□ □□□□ □□□□□ □□ □□□□ □□□□□□ □□□□□□ □□□□□ □□□□□□ □□□□□ □□□□□□□ □□□□□□□ □□□□ □□□□ □□ □□□□□□□ □□□□□ □□ □□□□□□□□□ □□ □□□□ 10 □□□□ □□□□□ □□□□ □□□□□ □□□□□□ □□□□□ □□□□ □□□□□□ □□ □□? □□□□□ □□□□ □□□□□□□ □□□□□ □□□□ 97/90 □□□□□ □□□□□ □□□□ □□□□ □□□□ □□□□ □□□□ □□□□□□□□ □30 □□□□ □□□□□□□□ □□□□□□ □□□□□□ □□□□□□ □□□□□□□□ □□□□ □□□□ □□□□□□□□ □□□□□□□ □□□□□ 3 □□ □□□□□□□□□□ □□□□□□ □□□□□ □□□□□ □□□□□□□ □□□□□□ □□□□□□□ □□□□□□□□ □□□□□□ □□□□□ □□□□ □□□□□ □□□□□ □□□□□□□ □□□□□□ □□□□ □□□□ □□□□ □□□□□□□ □□□□□ 24 □□ 1992 □.□ □□□□□□□□ □□□□□□ □□□□□ □□□□□□ □□□□□□□ □□□□□ □□□□□□□□□ □□ □□□□ □□□□□ □□□□ □□□□□□□□ □□□□□□ 10 □□□□ □□□□□ □□□□□ □□□□ □□□□□□□□ □□□□ □□□□ □□□□ □□□□□ □10 □□□□ □□

□□□ □□□ □□□□□□□ □□□ □□□ □□□□□□□ 10 □□□ □□□ □□□□ □□ □□□□□□ □□ □□□□□□□□□□ □□□ □□□□□ □□□ □□□□ □□□□□ □□□□□□□ □□ □□□□ □□□ □□□ □□□ □□□ □□□□ □□ □□□□□□□ □□□ □□□□ □□□□□ □□□□□ □□□□□ □□□ □/□□□ □□□□□□□□ □□ □□□ □□□□□ □□□□ □□□ □□□□□ □□□ □□□□ □□□ □□□□ □□□□□□□□□

□ □ □

1. □□/□/□□□ □/□□ □□/□ 78317 □□□□ 09 □□ 2000 □.□ □□□□□ □□/□□□□ □/□□ □□/□ 64469 □□ 05 □□ 2001 □.□ □□□□ □□□□□ □□/□/□/□/□ 348(1) □□□□ □□□□□□□□
2. □□□□ □□□□ □□ □□□ □□ 29 □□ 2001 □.□ □□□□ □□□□ □□□□ □□□□□□□□ □□□□ □□□□□□□□ □□□ □□□□□□□□ □□□□ □□□□□□□□ □□□□□ □□ □□□□□□□ □□□□□□ □□□ □□□ □□□□□□□

□/□

የሰ/መ/ቁ 45167

ጥቅምት 24 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ቦረን ሪል ስቴት አክሲዮን ማሕበር ጠበቃ አቶ ገመዳ ጎንፋ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ዋቅቶሌ ታዬ አቶ መሊሣ ኤጀታ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 73007 መጋቢት 17 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት በማያዝያ 6 ቀን 2001 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡

የክርክር መነሻ ተጠሪ በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በከሣሽነት ቀርበው የሁለት ዓመት የእረፍት ፈቃድ ወስጄ ስመለስ በሥራ ቦታዬ ሌላ ሠው ተቀጥሮ ስላገኘሁና እስካሁን ወደ ስራ መደቤ ሳይመልሱ እያጉላጉ ስለሆነና የደመወዝ ጭማሪም ስለከለከሉኝ አሠሪው በተዘዋዋሪ መንገድ የሥራ ውሉን ያቋረጠ ስለሆነ ወደ ሥራ እንዲመልሰኝ የደመወዝ ጭማሪ እንዲከፍለኝ እና የአመት እረፍት ወደ ገንዘብ ተለውጦ እንዲሰጠኝ ይህ የማይሆን ከሆነ በአማራጭ የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍል ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ተጠሪን ከሥራ አልተሰናበተም፡፡ የሠራበት የወር ደመወዝ ተከፍሎታል፡፡ የዓመት እረፍት እንዲወስድ

የተፈቀደለት በመሆኑ በገንዘብ ተለውጦ ይሰጠኝ የሚለው ተገቢ አይደለም። አመልካች ለሠራተኞች የደመወዝ ጭማሪ ያላደረገ በመሆኑ ጭማሪው ይሰጠኝ ብሎ የጠየቀው አላግባብ ነው። ድርጅቱ እስከ አሁን ድረስ የሥራ ውሉን ያላቋረጠ በመሆኑ ወደ ሥራ እንዲመለስ በማለት ያቀረበው ክስ የክስ ምክንያት የለውም በማለት የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ ይዞት በነበረው የሥራ መደብ ሠራተኛ የተቀጠረው ለተወሰነ ጊዜ ሥራውን ለመሸፈን ብቻ መሆኑን በማስረጃ ተረጋግጧል። ተጠሪ የሥራ ውሉ ባልተቋረጠበት ሁኔታ ወደሥራ እንዲመለስ በማለት ያቀረበው ክስ የህግ ድጋፍ የለውም። የደመወዝ ጭማሪ ስለመደረጉ ተጠሪ አላስረዳም በማለት የተጠሪውን ክስ ሙሉ በሙሉ ውድቅ በማድረግ ወስኗል።

ከፍተኛው ፍርድ ቤት በተጠሪ የቀረበውን ይግባኝና አመልካች የሰጠውን መልስ ከመረመረ በኋላ አመልካች ተጠሪ ከእረፍት ሲመለሱ ሥራ አልሰጣቸውም በሚል ምክንያት ተጠሪ ወደ ቀድሞ የሥራ ቦታቸው ተመልሰው እንዲሠሩና ያልተከፈለ ደመወዛቸውንም እንዲከፍል በማለት ወስኗል። አመልካች በዕሑፍ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የተጠሪ የሥራ ውል እንዳልተቋረጠ በበቂ ማስረጃ ተረጋግጦ እያለ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ከዚህ ተቃራኒ የሆነ ግምት መወሰዱ የህግ ድጋፍ የለውም። ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ ከሥራ ቦታው በራሱ ፈቃድ ጠፍቶ የቆየ መሆኑ ተረጋግጧል። ስለዚህ ተጠሪ ራሱ ከሥራ ቦታ ጠፍቶ ለቆየበት ጊዜ ሁሉ ያልሠራበትን ደመወዝ እንድንከፍለው የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 13(4) እና አንቀፅ 54(2) የሚቃረን በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባዋል በማለት አመልክቷል። ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የሥራ ውሉን አቋርጧል። የተሰጠኝን ፈቃድ ጨርሼ ስመለስ ሥራ አልሰጠኝም ስለዚህ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተገቢና የህግ ስህተት የሌለበት ነው።

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለው የሥራ ውል እስካአሁን ድረስ ያላቋረጠ መሆኑን የከፍተኛው ፍርድ ቤት በውሣኔው ገልጿል፡፡ አመልካች አሠሪ በመሆኑ የድርጅቱ ሠራተኛ የሆኑት ተጠሪ የሚሠሩት ሥራ አልሰጣቸውም በሚል ምክንያት ተጠሪ ሥራ ካቆሙበት ጀምሮ ያልተከፈለ ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈላቸው ወስኗል፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለውን የሥራ ውል ካላቋረጠ ተጠሪ ከሥራ ቦታ የሚጠፋበት በቂ ምክንያት የለም፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች የሥራ ውሉን ያላቋረጠና የተጠሪንም ደመወዝ ይከፍል እንደነበር የጥር ወር 2000 ዓ.ም ደመወዝ ተሠርቶ በደመወዝ መክፈያ ሠነድ ላይ እንደሚገኝ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ከሥራ ያልተሰናበቱ በመሆኑ ወደ ሥራዬ እንድመለስ ይወሰንልኝ ወይም የተለያዩ ክፍያዎች በአማራጭ ይከፈሉኝ ብለው ክስ የሚያቀርቡበት በቂ ምክንያት የላቸውም፡፡ ተጠሪ ከሥራ ቦታ ያልተገኙት በራሳቸው ፈቃድ እና ፍላጎት ውጭ በመሆኑ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ ላልሠራበት ጊዜ ያልተከፈለው ደመወዝ እንዲከፈለው በማለት የሰጠው ውሣኔ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 54(1) የተደነገገውን የሚቃረንና ተጠሪ በራሱ ጉድለት ለሥራ ዝግጁ ሆኖ በሥራ ቦታ ባለተገኘበት ጊዜ የቆረጠበትን የደመወዝ ክፍያ አመልካች አላግባብ እንዲከፍል የሚያስገድድ ውሣኔ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ውሣኔ ሠጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል
2. የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል
3. አመልካች ተጠሪ ያልሠራበትን ጊዜ ደመወዝ የመክፈል ግዴታ የለበትም ብለናል

4. አመልካች የተጠሪ የሥራ ልምዱ የትምህርት ዝግጅት እና የነበረውን የሥራ መደብና ደመወዝ ከግንዛቤ ውስጥ ባስገባ ሁኔታ መድቦ ማሠራት ይችላል ብለናል
5. ግራቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ

ይኸ ፍርድ በፊዴራል ጠቀላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰበር መ/ቁ 42805

ሐምሌ 6 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. ሐጎስ ወልዱ
2. ሂሩት መለሰ
3. ተሻገር ገ/ስላሴ
4. አልማው ወሌ
5. ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የአቶ ሞገስ በላቸው ወራሾች እነ ገነት ሞገስ (6 ሰዎች)
ጠ/ሥለሞን ተፈራ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. የአቶ ታደሰ ወ/ገብርኤል ወራሽ ተማሪ አማኑኤል ታደሰ
ጠ/ግርማ ቦጋለ ቀረቡ
2. ወ/ሮ ለተብርሃን ወ/ትንሳኤ - ቀረቡ

ፍ ር ድ

የ1ኛ ተጠሪ አውራሽ በአመልካቾች አውራሽና በ2ኛ ተጠሪ መሃከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል እንዲፈርስ ክስ መስርተው በዚሁ መሰረት በመወሰኑ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

የ1ኛ ተጠሪ አውራሽ በፌ/መ/ደረጃ ባቀረቡት ክስ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በጋብቻ በሚኖሩበት ጊዜ ያፈሩትን የጋራ መኖሪያ ቤት 2ኛ ተጠሪ የ1ኛ ተጠሪን ፈቃድ ሳይጠይቁ ለአመልካቾች አውራሽ ሰለሸጡላቸው የሽያጭ ውል እንዲፈርስላቸው ጠይቀዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪ መጥሪያ ደርሷቸው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌለበት የታየ ሲሆን የአመልካቾች አባት ባቀረቡት መልስ 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ሲሸጡላቸው ጋብቻ አልነበራቸውም ቤቱም የግላቸው በመሆኑ ውሉ ሊፈርስ የሚገባበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ የ1ኛ ተጠሪ አውራሽ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ጋብቻ ያላቸው ስለመሆኑ የጋብቻ ምስክር ወረቀት በማቅረብ ወይም የትዳር ሁኔታ መኖሩን በማስረዳት ስላላረጋገጡ ጋብቻ የለም፡፡

ጋብቻ ከሌለ ደግሞ የ1ኛ ተጠሪ አውራሽ ውሉ እንዲፈርስ ለመጠየቅ መብት የላቸውም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡

1ኛ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ በ1ኛ ተጠሪ አውራሽና በ2ኛ ተጠሪ መሃከል ጋብቻ መኖሩን የሚያስረዳ ማስረጃ እንዲቀርብ በስር ፍ/ቤት ተጠይቆ ሳይቀርብ በመቅረቱና ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት ሰነዱ መቅረቡ ተገቢ ነው በማለት ሰነዱን ካስቀረበ በኋላ በ1ኛ ተጠሪ አውራሽና በ2ኛ ተጠሪ መሃከል ጋብቻ መኖሩን ሰነዱ ስለሚያስረዳና 2ኛ ተጠሪ የ1ኛ ተጠሪን አውራሽ ፈቃድ ሳይጠይቁ የጋራ መኖሪያ ቤት ሊሸጡ ስለማይችሉ የሽያጭ ውሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት ግራ ቀኙ ወደነበሩበት እንዲመለሱ ሲል የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ ይህን ውሳኔ በመቃወም አመልካቾች ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው የነበረ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ውሳኔውን አፅንቶታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤታቱ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካቾች በቅሬታቸው የ1ኛ ተጠሪ አውራሽ ክስ ሲመሰርቱ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ጋብቻ ያላቸው ስለመሆኑ ያቀረቡት ወይም እንዲቀርብላቸው የጠየቁት ማስረጃ ሳይኖር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ማስረጃ እንዲቀርብ ተጠይቆ ታልፏል ያለው ስህተት ነው በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ቢሆን ተጠሪው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 345 መሰረት ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብላቸው ሳይጠይቁ ፍ/ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ማስረጃው እንዲቀርብ ማድረጉ ስህተት ነው፣ የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን በአግባቡ አጣርቶ አልወሰነም የሚል ከሆነ ጉዳዩን ወደስር ፍ/ቤት ሊመልሰው ሲገባ እራሱ አይቶ መወሰኑ ተገቢነት የለውም በማለት ውሳኔው እንዲሻርላቸው ጠይቀዋል፡፡ ይህ ችሎትም የሽያጩ ውል እንዲፈርስ መወሰኑ ከግራ ቀኙ ክርክር አኳያ በአግባብ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በማድረግ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ሰምቷል፡፡ 1ኛ ተጠሪ አባታቸው በክርክሩ ሂደት ማስረጃ እንዲቀርብላቸው የጠየቁ በመሆኑንና ፍ/ቤትም ትክክለኛ ነገር ለማግኘት ማስረጃ እንዲቀርብ ማድረጉ ስህተት የለውም ሲሉ 2ኛ ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ አውራሽ ጋር ተጋብተው ይኖሩ እንደነበር አስረድተዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔና የግራ ቀኙን ክርክር እንደመረመርነው በዚህ ጉዳይ ምላሽ የሚያስፈልጋቸው ጭብጦች በ1ኛ ተጠሪ አውራሽና በ2ኛ ተጠሪ መሃከል

ጋብቻ ነበር? አልነበረም? ነበር ከተባለ የሽያጭ ውሉ ሊፈርስ የሚገባበት ምክንያት አለ? የለም? የሚሉት ናቸው፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ ተጠሪዎች በ1ኛ ተጠሪ አውራሽና በ2ኛ ተጠሪ መሃከል ጋብቻ ነበር ሲሉ አመልካቾች በበኩላቸው ጋብቻ አልነበረም በማለት ክደው ተከራክረዋል፡፡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 258(1) እና 259(1) መሰረት ተከሳሽ የቀረበበትን ክስ አምኖ ሌላ አዲስ ነገር ህግ ወይም በከሳሹ አቤቱታ ያልተመለከተው አዲስ ነገር በመጥቀስ ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን የሚከራከር ካልሆነ በቀር በቅድሚያ ክርክሩን የሚጀምረውና ማስረጃ የሚያቀርበው ከሳሽ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የ1ኛ ተጠሪ አውራሽ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር አለኝ የሚሉት ጋብቻ በአመልካቾች ስለተካደ ጋብቻ ስለመኖሩ በቅድሚያ የማስረዳት ሸክም አለባቸው፡፡ የ1ኛ ተጠሪ አውራሽ በስር ፍ/ቤት ክስ ሲመሰርቱ ያቀረቡት ማስረጃ በ2ኛ ተጠሪና በአመልካቾች አውራሽ መኃከል የተደረገውን የቤት ሽያጭ ውል ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ውጪም ሌላ ማስረጃ እንደሌላቸው ገልፀዋል፡፡ በመሰረቱ ማንኛውም ተከራካሪ በእጁ የሚገኘውን ወይም ለማቅረብ የሚችለውን ወይም ለክርክሩ ይጠቅመኛል ብሎ የሚያምነው በፍ/ቤት ጥያቄም የሚቀርቡ ማስረጃዎችን ሁሉ በመጀመሪያው ቀነ ቀጠሮ ሊያቀርብ የሚገባው መሆኑን ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 137(1) መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም በመርህ ደረጃ ማስረጃዎች ሁሉ ሊቀርቡ የሚገባው በመጀመሪያ ቀነ-ቀጠሮ ነው፡፡ ነገር ግን ማስረጃዎችን በመጀመሪያ ቀነ ቀጠሮ በተከራካሪዎቹ ጉድለት ባልሆነ በቂ ምክንያት ሳይቀርቡ መቅረታቸውን ፍ/ቤቱ ሲረዳው በክርክሩ ሂደት ማስረጃው እንዲቀርብ ሊፈቀድ የሚችልበት ሁኔታ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 256 ስር ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የ1ኛ ተጠሪ አውራሽ ክስ ሲመሰርቱ ጋብቻ ስለመኖሩ ማስረጃ አላቀረቡም፤ እንዲቀርብም አልጠየቁም፡፡ ነገር ግን የመልስ መልስ በሚሰጡበት ጊዜ ጋብቻ መኖሩን የሚያስረዳ ማስረጃ ክሱን ባቀረቡበት ጊዜ ማግኘት አለመቻላቸው ገልፀው ማስረጃው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 256 መሰረት እንዲቀርብላቸው ጠይቀዋል፡፡ የስር ፍ/ቤት ግን ማስረጃው ያልቀረበው በከሳሽ ጉድለት ወይም በቂ ባልሆነ ምክንያት መሆን አለመሆኑን ሳይመረምርና ሊቀርብ የሚገባው መሆን አለመሆኑን ብይን ሳይሰጥ ማለፉን ተገንዝበናል፡፡ በሌላ በኩል 1ኛ ተጠሪ በከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሲያቀርቡ ማስረጃ እንዲቀርብላቸው ጠይቀው መታለፉን እንደ አንድ የቅሬታ ነጥብ አንስተዋል፡፡ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም

ማስረጃው እንዲቀርብ ተጠይቆ መታለፉ አግባብ አለመሆኑንና ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 345(1)(ሀ) እና (ለ) መሰረት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት መቀበል ሲገባው ያለበቂ ምክንያት ሳይቀበል የቀረውን ማስረጃ ወይም ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት ወይም ተገቢ መስሎ በታየው ጊዜ በማናቸውም ምክንያት ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ለማድረግ ይችላል፡፡ በተያዘውም ጉዳይ የስር ፍ/ቤት እንዲቀርብ የጠየቀው ማስረጃ እንዳይቀርብ ምክንያት ሳይሰጥ በማለፉና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ለትክክለኛም ውሳኔ አሰጣጥ ተገቢ መሆኑን ያመነበት ማስረጃ እንዲቀርብ ለማድረግ ከፍ ሲል የተጠቀሰው የስነ-ስርአቱ ድንጋጌ ስለሚፈቅድለት አመልካቾች ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ማስረጃውን እንዲቀርብ ማድረጉ ተገቢ አልነበረም በማለት ያቀረቡት ክርክር ህጋዊ መሰረት የለውም፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ማስረጃው በ1ኛ ተጠሪ አውራሽ እና በ2ኛ ተጠሪ መኃከል ጋብቻ መኖሩን እንደሚያስረዳ አረጋግጧል፡፡ ማስረጃውን በተመለከተ አመልካቾች በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጎ በማስረጃው አቀራረብ ላይ እንጂ በህጋዊነቱ ላይ ተቃውሞ እንደሌላቸው መግለፃቸውን በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ክርክር ከተደረገበት መዝገብ ተመልክተናል፡፡ በመሆኑም በ1ኛ ተጠሪ አውራሽና በ2ኛ ተጠሪ መሃከል ጋብቻ አለ በማለት የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የደረሰበትን መደምደሚያ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ በመርህ ደረጃ ደግሞ በጋብቻ ውስጥ ያለ ንብረት የተጋቢዎቹ የጋራ ንብረት ሆኖ የሚቆጥር በመሆኑ ንብረቱ የአንደኛው ተጋቢ የግል ንብረት ነው የሚል ወገን ይህንኑ የማስረዳት ሸክም አለበት፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት የ2ኛ ተጠሪ የግል ንብረት ነው የሚሉት በሁለቱ መሃከል ጋብቻ የለም በሚል ቢሆንም ጋብቻ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ ውጪ ጋብቻም ቢኖር በህጉ በተመለከቱ የተለያዩ ምክንያቶች ቤቱ የ2ኛ ተጠሪ የግል ንብረት ነው በማለት ያቀረቡት ክርክርና ማስረጃ ስለሌለ ቤቱ የግል ነው የሚለው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 68(ሀ) መሰረት የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመሸጥ የሁለቱም ተጋቢዎች ስምምነት የሚያስፈልግ ሲሆን አንደኛው ተጋቢ ፈቃዱን ሳይሰጥ ሌላኛው ተጋቢ ንብረቱን ሸጦ ከሆነ ፈቃዱን ያልሰጠው ተጋቢ ውሉ እንዲፈርስ የመጠየቅ መብቱ በአንቀፅ 69(1) ተጠብቆለታል፡፡ በተያዘውም

ጉዳይ የ1ኛ ተጠሪ አውራሽ የጋራ ንብረታቸው ሲሸጥ ፈቃዳቸውን ባለመስጠታቸው ውሉ እንዲፈርስ የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም በዚሁ መሰረት ውሉን ማፍረሱን ተገንዝበናል፡፡ በሌላ በኩል ግን የውሉ መፍረስ ውጤት ተዋዋዮች ወደነበሩበት ቦታ መመለስ መሆኑን ከፍ/ህ/ቁ 1815(1) ማየት የሚቻል ቢሆንም ውሉን በማፍረስ ተዋዋዮች ወደነበሩበት መመለስ የማይቻል ከሆነ ውሉን ለመፈፀም የተሰሩ ስራዎች ባሉበት እንዲቀሩ ማድረግ እንደሚገባ የፍ/ህ/ቁ 1816 ያመለክታል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የሽያጭ ውል የተደረገው በ1985 ዓ.ም መሆኑና ቤቱ እስካሁን በአመልካቾች ይዞታ መቆየቱን እንዲሁም ቤቱ ከተገዛ በኋላ ከፍተኛ ወጪ አውጥተው ቤቱን ያሻሻሉ በመሆኑ ወደነበሩበት ቦታ መመለስ የማይቻል ለመሆኑ አመልካቾች አጥብቀው ይከራከራሉ፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የ1ኛ ተጠሪ አውራሽ ፈቃድ ባለመኖሩ ውሉ እንዲፈርስ የወሰነው የሽያጭ ውሉ ከተደረገ በኋላ በአመልካቾች የተሰራ ነገር መኖር አለመኖሩና ቤቱ በተገዛበት ጊዜና በአሁኑ ወቅት ያለበት ደረጃ ሲታይ ውሉ ፈርሶ ግራ ቀኙ ወደነበሩበት ሁኔታ መመለስ የሚያስችል ስለመሆኑ ሳያረጋግጥ ነው፡፡ በመሆኑም ውለታውን ለመፈፀም የተሰራ ስራ ለማፍረስ የማይቻል ወይም አስቸጋሪ መሆን አለመሆኑ ሳይረጋገጥ ውሉ ፈርሶ ግራ ቀኙ ወደነበሩበት እንዲመለሱ መወሰኑ የህጉን ድንጋጌ ያላገናዘበ በመሆኑ መሰታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 26689 ህዳር 13 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 28012 ህዳር 29 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሻሽሏል፡፡
2. በ2ኛ ተጠሪና በአመልካቾች አውራሽ መሃከል የተደረገው የሽያጭ ውል ፈርሶ ግራ ቀኙን ወደነበሩበት መመለስ የሚቻል መሆን አለመሆኑ ከግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ተገቢው ይወስን ዘንድ ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) መሰረት ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት መልሰናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. የስር ፍ/ቤት መዝገቦች ይመለሱ፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።።

ራ/ታ

የሰበር መ/ቁ 44800

ጥቅምት 05 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. መንበረፀሐይ ታደሰ

2. ሂሩት መለሰ

3. ታፈሰ ይርጋ

4. አልማው ወሌ

5. ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ አብዱራዛቅ ሐሚድ - ጠ/አስቻለው አሻግሬ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ መንበረ አድማሱ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የመያዣ ውል ይፍረስልኝ ጥያቄ ነው፡፡ አመልካች ለፌ/መ/ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ሐሚድና ቤተሰቡ የግብርና ውጤቶች ኃ/የተ/የግ/ማህበር ከተጠሪ ላይ ለወሰደው ብድር አመልካች በኢ/አበባ ከተማ ወረዳ 23 ቀበሌ 12 ውስጥ የሚገኘውን ቤት በመያዣ ያስመዘገቡ ሲሆን አቶ ሐሚድ ይስሐቅ የተባለ ግለሰብም 2 ቤቶች በመያዣ ሰጥተዋል፡፡ ተበዳሪው ብድሩን አጠናቆ ባለመክፈሉ ባንኩ በመያዣ የያዛቸውን ቤቶች በሃራጅ ለመሸጥ በመንቀሳቀሱ ባንኩ የአቶ ሐሚድ ይስሐቅ ቤቶች በሐራጅ ሽጦ እዳውን በሙሉ ከፍሎ አጠናቋል፡፡ እዳው ተከፍሎ ስለተጠናቀቀ በመያዣ የሰጠሁት ቤት ካርታ እንዲመልስልኝ ብጠይቀው ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ የመያዣው ውሉ ከተፈረመ 10 አመት ያለፈው በመሆኑ ቀሪ ሆኗል፡፡ ስለዚህ ባንኩ ቤቴን በሐራጅ ለመሸጥ የጀመረውን እንቅስቃሴ እንዲያቆም የያዘውን ካርታ እንዲመልስ፣ ያልተከፈለ እዳ ካለ የሂሳብ መግለጫ እንዲያቀርብና ቀሪውን ገንዘብ ከፍዬ ቤቴ ከመያዣነት እንዲለቀቅልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ተበዳሪው የወሰደው ብድር ተከፍሎ ያልተጠናቀቀ በመሆኑና በፍ/ህ/ቁ 3058(1) የተመለከተው የ10 አመት ጊዜ ከማለፉ በፊት በመያዣ ንብረቱ ላይ እንቅስቃሴ የጀመረ ስለሆነ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ለፌ/ከፍተኛ

ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ፀንቶባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ዋነኛ አቤቱታ የመያዣው ውል ከተመዘገበ 10 አመት ስላለፈው በፍ/ህ/ቁ 3058(1) መሰረት መያዣው ቀሪ ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎትም ይህንኑ የአመልካችን ቅሬታ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በማድረግ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

አመልካች ሐሚድና ቤተሰቡ የግብርና ውጤቶች ኃ/የተ/የግ/ማህበር ለወሰደው ብድር ቤታቸውን በመያዣ ሰጥተዋል፡፡ የመያዣ ውሉም የተመዘገበው በ1987 ዓ.ም መሆኑን እንዲሁም ተበዳሪው ድርጅት ብድሩን መክፈል ባለመቻሉ ተጠሪ ለአመልካች ጥቅምት 24 ቀን 1992 ዓ.ም ማስጠንቀቂያ መስጠቱን አመልካች አልካዱም፡፡ አመልካች መያዣው ቀሪ ነው በማለት የሚከራከሩት የፍ/ሕ/ቁ 3058(1)ን በመጥቀስ ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ድንጋጌ መመልከት ያስፈልጋል፡፡ አመልካች የጠቀሱት ይህ ድንጋጌም እንደሚከተለው ይነበባል፡፡

የማይንቀሳቀስ ንብረት የመያዣ መብት ውጤት የሚኖረው ከተፃፈበት ቀን አንስቶ እስከ አሰር ዓመት ድረስ ነው፡፡

በዚህ ድንጋጌ መሰረት አንድ የመያዣ ውል ውጤት የሚኖረው መያዣው ከተመዘገበበት ቀን አንስቶ እስከ 10 አመት ድረስ ነው፡፡ በመሆኑም በመያዣ ውሉ ምክንያት በሚገኙ ማናቸውም መብቶች መገልገል የሚቻለው ይኸው የተወሰነው ጊዜ ከማለፉ በፊት ይሆናል ማለት ነው፡፡ ይህ የጊዜ ዘመን ሊራዘም የሚችለው 10 ዓመቱ ከማለፉ በፊት ውሉ እንዲታደስ አዲስ ምዝገባ ተከናውኖ ከሆነ ብቻ እንደሆነ ከፍ/ሕ/ቁ 3058(2) እንገነዘባለን፡፡ በመሰረቱ ይህ ህግ አመልካች እንደሚሉት የይርጋ ድንጋጌ አይደለም፡፡ ይርጋ ማለት በህግ ተለይቶ ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ በኋላ በአንድ ጉዳይ ክስ ለማቅረብ የሚከለከልበት የህግ ፅንሰ-ሃሳብ ነው፡፡ በመሆኑም ይርጋ አንድ ሰው በጉዳዩ ላይ መብት ያለው ቢሆንም እንኳን ይህንን መብቱን ለመጠየቅ የማይችልበትን ገደብ የሚመለከት ነው፡፡ ይህ ክልከላም ተፈፃሚ የሚሆነው ክስ ከቀረበ በኋላ ተከሳሹ የይርጋ መቃወሚያ አንስቶ የተከራከረ ከሆነ ነው፡፡ ከሳሽ ክስ የማቅረብ መብቱ በይርጋ ቀሪ ከሆነ በኋላ ክስ አቅርቦ ተከሳሽ ክሱ በይርጋ ቀሪ መሆኑን በመግለፅ ካልተቃወመ ክሱ ተቀባይነት አግኝቶ መታየት ይቀጥላል፡፡ የጊዜ ገደቡ በማለፉ ብቻ ፍ/ቤት የይርጋውን በራሱ አነሳሽነት

አንስቶ ክሱን ውድቅ ሊያደርግ አይችልም፡፡ የፍ/ሕ/ቁ 3058(1) የሚያስቀምጠው የይርጋን ጽንሰ-ሐሳብ አይደለም፡፡ የተጠቀሰው አንቀፅ የሚናገረው በህጉ የተመለከተው የጊዜ ገደብ ማለፍ የመያዣው ውሉን ቀሪ (lapse) የሚያደርገውና ከዚሁ ጊዜ በኋላ መያዣ ውሉ ተጠቃሚ የሆነው ሰው በመያዣው ላይ ያለው መብት የሚያበቃበትን ሁኔታ ነው፡፡ የመያዣ ውሉ ከተመዘገበ በኋላ 10 ዓመት ሆኖት እንደሆነና እንዲታደስ ካልተጠየቀ ጠያቂ ባይኖርም አቃቤ መዝገቡ መያዣውን እራሱ ሊሰርዘው እንደሚገባ የፍ/ሕ/ቁ 1632(2) ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም መያዣ ሰጪው 10 አመት በማለፉ መያዣው እንዲሰረዝ ጥያቄ ባያቀርብም መዝጋቢው አካል ራሱ ምዝገባውን ሰርዞ መያዣውን ቀሪ ሊያደርገው ይገባል፡፡

በሌላ በኩል መያዣው ነሐሴ 17 ቀን 1987 ዓ.ም የተመዘገበ ቢሆን በመያዣ የተያዘው ቤት አመልካች ክስ እስከመሰረቱበት ህዳር 12 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ አለመሸጡን ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡ አመልካችም ይህንኑ ጊዜ መሰረት አድርገው ነው መያዣው ቀሪ ነው ሲሉ የሚከራከሩት፡፡ ተጠሪ በበኩሉ መያዣው ከተመዘገበ በኋላ ተበዳሪው እዳውን ባለመክፈሉ 10 አመቱ ሳያልፍ ጥቅምት 24 ቀን 1992 ዓ.ም ማስጠንቀቂያ ለአመልካች በመስጠቱ መያዣው ቀሪ አልሆነም ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካች የተባለው ማስጠንቀቂያ የደረሳቸው መሆኑን አልካዱም፡፡ ክርክራቸው ማስጠንቀቂያ በመስጠት የይርጋ ጊዜን ማቋረጥ የሚቻለው ለዋና እዳ እንጂ ለማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ አይደለም የሚል ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከትነው በፍ/ህ/ቁ 3058 ስር የተቀመጠው የጊዜ ገደብ የይርጋ ጊዜ ገደብ ባለመሆኑ ስለይርጋ ማቋረጫ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ በሌላ በኩል ግን ባለገንዘቡ የመያዣ ውሉ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ 10 ዓመት ከማለፉ በፊት በመብቱ መገልገል ጀምሯል ሊባል የሚችለው መቼ ነው? የሚለው ሊታይ ይገባል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት ለሰጠው ብድር መያዣ የያዘ ባንክ ብድሩ ካልተከፈለው የ30 ቀናት ማስጠንቀቂያ በመስጠት ንብረቱን ለመሸጥና የባለቤትነት ስሙን ለገዢ ለማስተላለፍ እንደሚችል በቁጥር 3 ስር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ባንኮች የመያዣ መብታቸውን መገልገል የሚጀምሩት ማስጠንቀቂያ በመስጠት ለመሆኑ ከዚህ ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ቢሆን ተጠሪ ለአመልካች ጥቅምት 24 ቀን 1992 ዓ.ም ማስጠንቀቂያ በመስጠት በመብቱ መገልገል ጀምሯል፡፡ መያዣው ከተመዘገበበት ጊዜ ጀምሮ ሲቆጠር ደግሞ

ማስጠንቀቂያ የተሰጠው 10 ዓመት ሳያልፍ ነው፡፡ ተጠሪ ማስጠንቀቂያ ከሰጠ በኋላ ቤቱን ሳይሸጥ የ10 ዓመቱ ጊዜ አልፎ ሊሆን ይችላል፡፡ የቤቱ ሽያጭ ሳይጠናቀቅ 10 አመቱ ማለፉ ብቻውን ግን መያዣውን ቀሪ አያደርገውም፡፡ ሊታይ የሚገባው ተጠሪ በመብቱ መገልገል የጀመረበት ጊዜ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ሲታይ ደግሞ መያዣው ቀሪ የሚሆንበት የህግ መሰረት የለም፡፡ በዚህም ምክንያት የስር ፍ/ቤቶች የአመልካችን ክስ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለው ለማለት አልተቻለም፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 78317 ታህሳስ 09 ቀን 2000 ዓ.ም እንዲሁም የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 64469 ጥር 05 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔዎች በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንተዋል፡፡
2. ውሳኔው ስለፀና ይህ ችሎት ሰኔ 29 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ትዕዛዙ ለሚመለከተው ክፍል ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ